(ዓመታዊ መጽሔት)
2015

# ብርታት
# BIRTAT

“የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ በመማር የመስማት የተሳናቸውን ተካታችነት እንደግፍ”።



የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማህበር

ETHIOPIAN NATIONAL ASSOCIATION OF THE DEAF

## 50ኛ ዓመት



# የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው
# ብሔራው ማኅበር

የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኅበር ከአንጋፋ የአካል ጉዳተኞች ማኅበራት ቀደምት ሲሆን የተመሠረተው በመስከረም ወር 1963 ዓ.ም ነው፡፡ ማኅበሩ የዓለም መስማት የተሳናቸው ፌድሬሽንና የኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኞች ማኅበራት ፌድሬሽን መስራች ዓባል ነው፡፡ በመላ ሀገሪቱም ከ30 በላይ ቅርንጫፎች ሲኖሩት ቁጥራቸው ከ3.5 ሚሊየን በላይ እንደሆነ የሚገመተው መስማት የተሳናቸው ኢትዮጵያውን ይወክላል፡፡

## የማኅበሩ ርዕይ

ከመረጃና ተግባቦት ተግዳሮቶች ነጻ የሆነችና መስማት የተሳናቸው ዜጎችን በእኩልነት ያካተተች ኢትዮጵያ ዕውን ሆና ማየት፡፡

## የማኅበሩ ተልእኮ

በኢትዮጵያ ውስጥ ስለመስማት መሳን ትክክለኛ አመለካከት እንዲኖር ግንዛቤ በመፍጠርና ከመስማት ስነት ጋር የተያያዙ አሉታዊ አመለካቶችን በሂደት በማጥፋት፣ የትምህርትና የጤና አገልግሎቶች ለመስማት የተሳናቸው ተዳራሽ እንዲሆኑ በመሥራት፣ የመስማት የተሳናቸውን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዓቅም በመገንባት፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ እንዲጠና፣ እንዲሠነድ፣ እንዲስፋፋና ማኅበረሰባዊና ሕጋዊ እውቅና እንዲያገኝ በመሥራት መስማት የተሳናቸው ኢትዮጵያውያን ራሳቸውን እንዲችሉና አምራች ዜጎች እንዲሆኑ ማብቃት፡፡



*በዓል አዘጋጅ ኮሚቴ*

# ብርታት

የዓለም አቀፍ መስማት የተሳናቸው ሳምንት በዓል አስመልክቶ በየዓመቱ በኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኅበር የሚታተም እና በነፃ የሚታደል መጽሔት ፡፡


**አዘጋጆች**
ዶ/ር ጳውሎስ ካሡ
አቶ ሰይፉ ይልማ
አቶ ንጉሤ ሞገስ
ወ/ሪት ሶስና ዘውዴ
አቶ ፍቃዱ አሰፋ

**አስተርጓሚ**
ወ/ሮ እቴቱ ባየልኝ
አቶ ዳዊት ጎሳዬ

**የኮምፒውተር ጽሑፍ**
ወ/ሮ እቴቱ ባየልኝ

**ግራፊክስ ዲዛይነር**
አስቴር ንጉስ

**የበአል አዘጋጅ ኮሚቴ**
ዶ/ር ጳውሎስ ካሡ
ወ/ሪት ሶስና ዘውዴ
አቶ ጥላሁን በነበሩ
አቶ ዓለማየሁ ተፈሪ
አቶ አበበ ታምራት
አቶ ሠይፉ ይልማ
ወ/ሮ አመወርቅ መስፍን
ወ/ሮ ሕይወት ጌታቸው


## ማውጫ


2 | የአዘጋጆቱ መልእክት
የማኅበሩ ፕ/መልእክት | 3
4 | የሥራ አሥኪያጅ መልእክት
የሴቶችና ሕጻናት ሚ/ር መልእክት | 5
6 | የመረጃ ቋት
ከታሪክ ማኅደር | 7
15 | እናመሰግናለን
ዳሠሣ | 18
25 | አርአያዎችን
እናስታውሳችሁ | 28
32 | ሚዲያዎች ምን አሉ?
በጨረፍታ | 39
41 | ከፎቶ ማኅደር
Message from the President | 43
44 | Accessibility Matters That Affect The Deaf On A Daily Basis

# የአዘጋጆች መልእክት

የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኀበር ከዛሬ 52 ዓመታት በፊት መስከረም 3 ቀን 1963 ዓ.ም በአዲስ አበባ ተመሰረተ። በአህጉረ አፍሪካ አንጋፋ ከሆኑት መሰል ማህበራት ግንባር ቀደሙ ሲሆን የአለም መስማት የተሳናቸው ፌዴሬሽን መደበኛ አባል የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማኅበራት ፌደሬሽን መስራች ነው። ባለንበት ወቅት በአገሪቱ ክልሎች ከ27 በላይ ጽ/ቤቶች በመክፈት የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ዜጎች ሁለንተናዊ መብት ለማስከበርና ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ በመስራት ላይ ይገኛል።

የአለም አቀፍ መስማት የተሳናቸው ፌዴሬሽን ምስረታን ምክንያት በማድረግ እ.ኤ.አ በመስከረም ወር መጨረሻ በአባል አገራቱ የሚከበረው አለም አቀፍ መስማት የተሳናቸው ሳምንት ለ29ኛ ጊዜ በአገር አቀፍ ደረጃ ሲያከብር ቆይቷል።

ከዛሬ 2 ዓመታት በፊት ማህበሩ የተመሰረተበትን 50ኛ ዓመት ለማክበር ደፋ ቀና በሚልበት ወቅት በዓለማችን የተከሰተው የኮሮና ወረርሽኝ እንዲሁም ሰው ሰራሽ ግጭቶች ሳቢያ ውጥኑን ለማከናወን እንዳይችል እንቅፋት ሆኖበታል። ይሁን እንጂ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የ50 ዓመታት ጉዞውን መዘከር ባይችልም ከዓመታት በፊት የወጠነውን እቅድ ዛሬ ላይ ለመከወን በድጋሚ ዘግየት ብሎ ቢሆንም ቁርጠኛ በመሆን ተነስቷል።

የበዓሉ መከበር ከታሪካዊነቱ ባሻገር ለማኅበሩ የሚኖሩት ጠቀሜታዎች መካከል አንዱ የመስከረም ወር ማኅበሩ የተመሰረተበት መሆኑን ለአብነት ያህል መጥቀስ ይቻላል። በአሉም ከሚያስገኘው ዘርፈ ብዙ ሁነቶች በአጋጣሚው ተጠቅሞ ለመንግስት ድምፁን እንዲያሰማ ሁነኛ መድረክ ከመሆኑ ሌላ የማህበረሰቡን የተዛባ አመለካከት በመለወጥ አለመስማት አለመቻል እንዳልሆነ በማሳየት በኩል ጉልህ ሚና ይጫወተል።

የዘንድሮው ክብረ በዓል በልዩ ልዩ ክንውኖች የሚከበር ሲሆን ድምቀት በመስጠት መልዕክቱን ከሚያስተላልፍባቸው መሳሪያዎች አንዱና ዋነኛው "ብርታት" በሚል ስያሜ የሚያሳትመው መጽሔት ይገኝበታል።መጽሔቱ ካለፉት ጥቂት ዓመታት በፊት ለህትመት መብቃት ሳይችል ቢቀርም እነሆ! ዛሬ ላይ ልዩ ልዩ መልዕክቶች አንግቦ በድጋሚ ስያሜውን ሳይለቅ ተከስቷል። በውስጡም የተለያዩ መልዕክቶች አስተማሪና አዝናኝ ጽሁፎች አካቶ አምሮና ተሞሽሮ ለህትመት መብቃቱ የምስራች እንደመሆኑ የመስማት የተሳናቸው እምቅ ችሎታ ጎልቶ የሚስታዋልበት እንዲሆንና ጉልህ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ተስፋ እናደርጋለን።



የመጽሔት ዝግጅት ኮሚቴ በከፊል

# የብሔራዊ ማኅበሩ ፕሬዚዳንት መልእክት


ጳውሎስ ካሱ አበበ (ዶ/ር)

በመስከረም ወር 1963 ዓ.ም. የተመሠረተው የኢትዮጵያ መስማት የተሰናቸው ብሔራዊ ማኅበር የወርቅ ኢዩቤልዩውን እያከበረ ነው፡፡ ስለመስማት የተሰናቸው የነበረው አመለካከት አሉታዊ በነበረበትና ማኅበር ማቋቋም በመንግሥት በበጎ መልኩ በማይታይበት ፈታኝ ዘመን በጥቂት አርቆ አሳቢ ግለሰቦች በሱቆችና ካፌ በመሰብሰብ የተጀመረው ማኅበር ዛሬ በመላ ሀገሪቱ ከ29 በላይ ቅርንጫፎች ያሉትና ከ3.5 ሚሊዮን በላይ እንደሆኑ የሚገመቱትን መስማት የተሰናቸው ኢትዮጵያውያን የሚወክል ጠንካራ ማኅበር ለመሆን በቅቷል፡፡ የሃምሳ አመታት ጉዞውም በእጅጉ ፍሬያማና በስኬት የታጀበ ጉዞ ነበር፡፡ ዛሬ መስማት የተሰናቸው ኢትዮጵያውያን የተጎናጸፏቸው የትምህርትና የሥራ እድሎች፣ የጤናና የማሕበራዊ አገልግሎቶች ወዘተ የማኅበሩ የኅምሳ አመታት ትግል ፍሬዎች ናቸው፡፡ ይህን ስኬት ስናከብር የማኅበራችንን መስራቾች እንዲሁም በማኅበሩ ታሪክ ውስጥ የድርሻቸውን እየተወጡ ማኅበሩን ለዛሬ ያደረሱትን ሁሉ እንዲሁም የማሕበሩን አጋሮች ውለታ በማሰብና ልባዊ ምስጋና በማቅረብ ነው፡፡

እያከበርን ያለነው የማኅበራችንን የወርቅ ኢዩቤልዩ ብቻ ሳይሆን በአለም አቀፍ ደረጃ ለ64ኛ ግዜ በሀገራችን ለ30ኛ ግዜ የሚከበረውን አለምአቀፍ የመስማት የተሰናቸው ህዝቦች ሳምንት (IWDP) ጭምር ነው፡፡ የዚህ አመት የIWDP መሪቃል "ሁሉን አካታች የሆኑ ማኅበረሰቦች እንገንባ!" የሚል ነው ይህን መሪቃል ከማኅበራችን 50ኛ አመት ክብረበአል ጋር በማጣመር "ሁሉን አካታች የሆኑ ማኅበረሰቦች በመገንባት የ50 አመት ድሎቻችንን አጠናክረን እናስቀጥላለን" በሚል መሪ ቃል እናከብራለን፡፡ የማሕበራችን የ50 ዓመታት ትግል ዋና ግብ የመስማት የተሰናቸው ዜጎች ሁለንተናዊ ተካታችነት ማረጋገጥ በመሆኑ ይህ መሪ ቃል ወቅታዊ ነው፡፡ እስካሁን ለተገኘው ውጤት ልባዊ ምስጋና እያቀረብን የተጀመረው ማካተት ቀጥሎ መስማት የተሰናቸውን ያለምንም አድልኦ የሚያካትት ማኅበረሰብ እስኪፈጥር የሚመለከታቸው ሁሉ ከጎናችን መቆማቸውንና የበኩላቸውን ማድረግ እንዲቀጥሉ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡ ለተወሰኑ አመታት ተቋርጣ የነበረችው ብርታት መጽሔታችንንም በዚህ እትም በመመለሷ ደስታችንን እጥፍ ድርብ አድርጎታል፡ ፡ የማኅበራችንን አባላትና አጋሮች ሁሉ እንኳን ለ50ኛ አመት በዓላችን አደረስን እያልኩ መጪው ግዜ የተሻለ ስኬት የሚመዘገብበትና አካታች ማኅበረሰብ የሚፈጠርበት እንዲሆን መልካም ምኞቴን እገልጻለሁ፡፡

# የብሔራዊ ማኅበሩ ሥራ አሥኪያጅ መልእክት




አመለወርቅ መስፍን

የዓለም መስማት የተሳናቸው ፌዴሬሽን ምሥረታን ምክኒያት በማድረግ በየዓመቱ መስከረም ወር መጨረሻ በዓባል ሀገራት ዘንድ የዓለም ዓቀፍ መስማት የተሳናቸው ሳምንት በዓል ተከብሮ ይውላል፡፡ በዓለም ለ64ኛ ጊዜ በአገራችን ለ30ኛ ጊዜ በተለያያዩ መርሐግብሮችና መሪ ቃላት ሲከበር ቆይቷል፡፡ ዘንድሮ የሚከበረውን መስማት የተሳናቸው ሳምንት ከሌሎቹ ለየት የሚያደርገው ባለፉት ሁለት ዓመታት ማኅበሩ የተመሠረተበትን 50ኛ ዓመትን በኮሮና ወረርሽኝ እንዲሁም በሀገራችን በተከሰተው ግጭቶች ሳቢያ ሳይከበር ቆይታል ፡፡

የዘንድሮ የዓለም መስማት የተሳናቸው ሳምንት እንዲሁም ብሔራዊ ማኅበሩ የተመሠረተበት 50ኛ ዓመት “ሁሉን አካታች የሆነ ማኅበረሰቦችን በመገንባት የ50ዓመት ድሎቻችንን አጠናክረን እናስቀጥላለን” በሚል መሪ ቃል እያከበርን እንገኛለን፡፡ ብሔራዊ ማኅበሩ ላለፉት 50 (ኀምሳ) ዓመታት የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው መብትና ጥቅሞች ለማስከበር ያለሰለሰ ጥረት ሲያደርግ ቆይታል፡፡

በእነዚህ ዓመታት ያስገኛቸው የጥረቱ ቱሩፋቶች ማስታወስና መዘከር ለቀጣዩ ትውልድ የሚተላለፍ አሻራ ከመሆኑም ባሻገር ቀጣይ የቤት ሥራዎችንም የማስረከብ አደራ ነው፡፡ መስማት የተሳናቸው ከቅድመ መደበኛ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ድረስ መማር እንዲችሉ በሁሉም ት/ቤት የምልክት ቋንቋ የአስተርጎሚ አገልግሎት እንዲያገኙ መረጃ በቴሌቪዥን በምልክት ቋንቋ እንዲደርሳቸው የማድረግ ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል ተችሏል፡፡ ብሔራዊ ማህበሩ ከ29 በላይ ቅርንጫፎች በተጨማሪ መስማት የተሳናቸው መዋዕለ ሕጻናት ት/ቤት በማስተዳደር ላይ ይገኛል፡፡በዚህ አጋጣሚ ሳልጠቅሰው ማለፍ የማፈልገው ከዚህ በፊት የብሔራዊ ማኅበሩ  የነበረው መሬት ለመስጊድ መሥሪያ እንዲሆን በመደረጉ እንዲሆም በዓሁኑ ወቅት በሂደት ላይ ያለው ወንዝ ዳር ፕሮጀክት የመስማት የተሳናቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች በተለይም ወጣቶች የተለያዩ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች የሚያደርጉበት እና የተለያዩ ጉዳዮች ላይ የሚወያይበት አዳራሽ እንዳያሳጣን ሥጋት አለ፡፡

በአሁኑ ወቅት መንግሥት ለአካል ጉዳተኞች ልዩ ትኩረት ሠጥቶ በመሥራት ላይ በመሆኑ የማኅበሩ ያለበትን የቦታ እጥረት ለመቅረፍ እገዛ ሊያደርግለት እንደሚገባ ለማሳሰብ እወዳለሁ፡፡ ሐሳቤን ሳጠቃልል ለብሔራዊ ማኅበሩ 50ኛ ዓመት መከበር በገንዘብ በዕውቀት፣ ጊዜና ጉልበታቸውን በመሠዋት አስተዋጽ™ ላበረከቱ አካላት በሙሉ በጽ/ቤቱና በራሴ ስም ምስጋናዬን እያቀረብኩ ለመላው መስማት የተሳናቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሁ ለብሔራዊ  ማኅበሩ መስራቾች እንኳን ለብሔራዊ ማኅበሩ 50ኛ የወርቅ እዮቬልዩ በዓልና መስማት የተሳናቸው ሣምንት አደረሳችሁ ለማለት እወዳለሁ፡፡

# የኢፌዲሪ የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒሥቴር ሚኒሥትር መልእክት


ዶ/ር ኤርጎጌ ተስፋዬ

በቅድሚያ እንኳን ለብሔራዊ ማህበሩ 50ኛው የወርቅ ኢዮቤልዩ የምስረታ በዓል በሰላም አደረሳችሁ፣ አደረሰን ለማለት እወዳለሁ። ሁላችንም እንደምናውቀው ማንም ሰው አካል ጉዳተኛ ላለመሆን ምንም ዓይነት ዋስትና የለውም። አካል ጉዳተኛነት በማንኛውም ሁኔታ፣ ጊዜና ስፍራ እንዲሁም በማንኛውም ሰው ላይ ከጽንሰት እስከ ህልፈት ሊደርስ ወይም ሊከሰት የሚችል አንዱ የህይወት አጋጣሚ እንደሆነ በማስተዋል ሁላችንም ለአካል ጉዳተኞች መብት መጠበቅና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ልንረባረብ ይገባል።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማህበር ጋር በቅንጅት በመስራት ላይ ሲሆን ማህበሩ ከተቋቋመበት ዓላማ አንጻር መስማት የተሳናቸውን ኢትዮጵያውያን በፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ተሳትፏቸዉ እንዲጎለብት፣ መብትና ግዴታቸውን እንዲገነዘቡና በየዘርፉ በተደራጀ አግባብ ሁለገብ አቅማቸውን በማጎልበት በሃገር አቀፍ ደረጃ በተዘረጉ የልማት ፕሮግራሞችና ልዩ ልዩ አገልግሎቶች እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል በትጋት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ አንጋፋ ማህበር መሆኑን መግለጽ እወዳለሁ ።

ማህበሩ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ከፍቶ በትምህርት ዘርፍ መስማት ለተሳናቸው ህጻናት ቅድመ መደበኛ ትምህርት በመስጠት ላይ ሲሆን ለመደበኛ አካቶ ትምህርት የሚያበቃቸውን መሰረታዊ እውቀትና የምልክት ቋንቋ ስልጠና በመስጠት ከሚመለከታቸው አጋር ድርጅቶችና ማህበራት ጋር በመተባበር የምልክት ቋንቋ እንዲስፋፋ እያደረገ ያለው ተግባር ሊበረታታ ይገባል።

በተለይም የምልክት ቋንቋ መግባቢያ እንዲሆን በትምህርት ተቋማት፣ በሚዲያና በህብረተሰቡ ውስጥ እንዲሰርጽና የአካቶ ትምህርት ትግበራና የስነተዋልዶ ጤና እንዲሁም የተላላፊ በሽታዎች የጥንቃቄና መከላከል ትምህርት አገልግሎት ላይ እንዲውል እንዲሁም መስማት የተሳናቸው ዜጎች ባህል እንዲስፋፋና እውቅና እንዲያገኝ በማህበሩ እየተደረገ ያለው ጥረት ይበል የሚያሰኝ ነው።

አካል ጉዳተኞች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ሚና በማጎልበት ለሚኖሩበት ማህበረሰብ እድገትና ኢኮኖሚያዊ ልማት የበኩላቸውን አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ በጋራ እንድንረባረብ ጥሪዬን እያቀረብኩ ከምስረታው ጀምሮ ከኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማህበር ጎን ለቆማችሁና ሁለገብ ድጋፍ በማድረግ ላይ ለምትገኙ አጋር አካላት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና በራሴ ስም እያመሰገንኩ በሃገራችን ለ30ኛ ጊዜ **“ ሁሉን አካታች የሆነ ማህበረሰብ በመገንባት የ50 ዓመት ድሎቻችንን አጠናክረን እናስቀጥላለን!! “** በሚል መሪ ቃል ለሚከበረው መስማት የተሳናቸዉ ቀን እና ለማህበሩ 50ኛ ዓመት የወርቅ ኢዮቤልዩ የምስረታ በዓል እንኳን በሰላም አደረሳችሁ ለማለት እወዳለሁ!!!

እግዚአብሔር ኢትዮጵያን እና ህዝቦቿን ይባርክ !!!

# ከመረጃ ቋት

የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማህበር ከአውስትሪሊያ ኤምባሲ በተገኘ አካሌና ሙብቶቹ የመስማት ስነቴ በሚል ፕሮጀክት አነስተኛ ድጋፍ በ18 (አስራ ስምንት) የማህበሩ ቅርንጫፎች እየተገበረ ይገኛል፡፡ ይህ ፕሮጀክት እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በጥር ወር 2022 የተጀመረ ሲሆን አንደኛ ዙር ትግበራውን በጥሩ ሁኔታ በማጠናቀቁ የ2ኛ ዙር ትግበራ ላይ ይገኛል፡፡

የዚህ ፕሮጀክት ዓላማ ከ4 ዓመት በፊት የሴቶች አቅም ግንባታ እና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መከላከል ፕሮጀክት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን የያኔው ፕሮጀክት በፊላንድ ኤምባሲና መንግሥት የሚደገፍ ነበር፡፡ በፊላንድ ኤምባሲና መንግሥት ይደገፍ የነበረው ፕሮጀክት በማህበሩ ሥር ባሉ 30 (ሰላሳ) ቅርንጫፎች ቡና ጠጡ የሚል መርሐ ግብር እያዘጋጀ በመርሐ ግብሩም የአቻ ለአቻ ውይይት እያደረጉ ግንዛቢያቸውን የሚያሳድጉበት መርሐ ግብር ነበር፡፡ ያ መርሐ ግብር ሁላችንም የምናስታውሰው ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ በአውስትራሊያ መንግስት ድጋፍ የተከናወነ ያለው ፕሮጀክት በዓላማና በይዘት ከበፊቱ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ይህም ፕሮጀክት በአሁኑ በ18 ቅርንጫፎች ማለትም በአዳማ፣ ደብረ ብርሃን፣ ነቀምት፣ አምቦ፣ ዲላ፣ ሐዋሳ፣ ፍኖተ ሰላም፣ ባህር ዳር፣ ሻሸመኔ፣ አለታ ወንዶ፣ ወላይታ፣ ሆሳዕና፣ ሐረር፣ አርባ ምንጭ፣ ጅማ፣ እንዲሁም በሁለት የከተማ አስተዳደር ሲሆኑ ከተሞች አዲስ አበባና ድሬደዋ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ይህ ፕሮጀክት የሚተገበርባቸው ክልሎችና ከተሞች ቢኖሩም በሀገራችን በተከሰተው የፀጥታ ችግር ምክንያት ፕሮጀክቱ የፀጥታ ችግር ባሉባቸው ከተሞች ሊተገበር አልቻለም፡፡

የዚህ ፕሮጀክት ተጠቃሚዎች ወጣት ወንዶችና ሴቶች ናቸው፡፡ በእያንዳንዱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች 2 (ሁለት) አስተባባሪዎች አሉ፡፡ በእነዚህ አስተባባሪዎች በኩል ቡና ጠጡ ፕሮግራም ይደረጋል፡፡ በዚህ ፕሮግራም ሰዎችን በመጋበዝና የአቻ ለአቻ ውይይት በማድረግ ስለ ሥነ.ተዋልዶ ጤናና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ግንዛቤያቸው እንዲዳብር ይደረጋል፡፡

የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኅበር እየሠራቸው ያሉ ሥራዎች ከብዙ በጥቂቱ

- ብሔራዊ ማህበሩ ከአውስትራሊያ ኢምባሲ መስማት የተሳናቸው ሴቶችና ልጃገረዶች ሰብዓዊ መብትና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ስልጠና ለማዘጋጀት በማህበሩ ፕሬዝዳንት ሃሳብ አመንጭነት ተዘጋጅቶ የቀረበው የፕሮጀክት ፕሮፖዛል እየተገበረ ይገኛል፡፡
- ለባለድርሻ አካላት የምልክት ቋንቋ ስልጠና በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡
- ብሔራዊ ማህበሩ መስማት የተሳናቸውን ዜጎች በትምህርት፣በጤና ተቋማት፣እና በልዩ ልዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ እኩል ተጠቃሚ የሚሆኑበትን መንገድ ማመቻቸት እየሰራ ይገኛል፡፡
- ለአዲስ አበባ ከተማ ከተለያዩ ክፍለ ከተሞች ለተወጣጡ የፖሊስ አባላት መሠረታዊ የምልክት ቋንቋ ስልጠና ተሰጥታል፡፡
- ለአዲስ አበባ ከተማ ለሚኖሩ መስማት ለተሳናቸው ተማሪ ወላጆች መሰረታዊ የምልክት ቋንቋ ስልጠና ተሰጥታል፡፡
- በብሔራዊ ማህበሩ ውስጥ እንዲያገለግሉ የተቀጠሩ አዲስ ሰራተኞች ስራቸውን ከመስማት የተሳናቸው ሰራተኞች እና ተገልጋዮች በተሳካ መልኩ እንዲያከነውኑ መሰረታዊ የምልክት ቋንቋ ስልጠና ተሰጥታል፡፡
- ቋንቋ ለማያውቁ መስማት የተሳናቸው አባላት በየሳምንቱ ቅዳሜና እሁድ መሰረታዊ የምልክት ቋንቋ ስልጠና እየተሰጠ ይገኛል ፡፡
- በአዲስ አበባ ከተማ ለሚኖሩ መስማት የተሳናቸው ህጻናት የራሱን ት/ቤት ከፍቶ ለተማሪዎች የደንብ ልብስ፣ምገባ ከክፍያ ነጻ በመስጠት ላይ ነው፡፡
- መስማት የተሳናቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውቅት የሚገጥማቸውን የተግባቦት ችግር ለመቅረፍ ለፍርድቤቶች ፣ውልና ማስረጃ የትርጉም አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

# የኢመየብማ ታሪክ ባጭሩ

**ከማኅበሩ ድረ-ረጽ (http://www.enadet.org)**
**መስከረም 28 ቀን 2015 ዓ.ም.**
**የኢመየብማ ታሪክ**



*“መስማት የተሳናቸው ሰዎች ላለባቸው የጋራ ችግሮች ለመዋጋትና ለዚህ ማኅበር አንድ ላይ ቆምን። ” በመስከረም 1963 ዓ.ም በቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስትያን ማኅበሩን ለመመሥረት የተሰበሰቡ መስማት የተሳናቸው ሰዎች ቡድን (1963 ዓ.ም.) (ፎቶ: ከማኅበሩ መዝገብ ቤት)*

## ከየት ወደ የት?

የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኅበር ከመቋቋሙ በፊት መስማት የተሳናቸው ብዙ ችግሮች ነበሩባቸው። ሕብረተሰቡ መስማት የተሳናቸውን ሰዎች መማር አይችሉም የሚል አተያይ ነበረው። መስማት የተሳነው ሰው በአማርኛ ቋንቋ ”ደንቆሮ” ተብሎ ይጠራ ነበር። ይህም ማለት ያልተማረ ወይም ሊማር የማይችል የሚል ትርጉም ነበረው። ለሥራ ስምሪት እና ሌሎች ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ዕድሎችም አልነበሩም። በመንግስት የሚተዳደሩ የዓይነ ሥውራን አዳሪ ትምህርት ቤቶች የነበሩ ቢሆኑም ለመስማት የተሳናቸው ግን በመንግሥት የሚተዳደር ምንም ነገር አልነበረም። በአዲስ አበባ ውስጥ ሁለት፣ ከረን፣ ኤርትራ ውስጥ ደግሞ አንድ የመስማት የተሳናቸው ትምህርት ቤቶች የነበሩ ቢሆኑም፣ እነዚህ ትምህርት ቤቶች ዋና ዓላማቸው ሃይማኖት ማስተማር በሆነ ከውጭ በመጡ ሚስዮኖች ተከፍተው የሚሠሩ ነበሩ።

አንዳንድ ቤተሰቦች መስማት የተሳነው ልጅ መውለድ ከእግዚብሔር እንደመጣ ርግማን ጋር ማገናኘታቸው እንግዳ ነገር አልነበረም። መስማት ለተሳነው ልጅ መውለድ ርግማን ነው የሚለው የሕብረተሰቡ አሉታዊ አመለካከት ለአንዳንድ ቤተሰቦች መስማት የተሳናቸው ሕፃናትን ከሕዝብ እይታ ለመደበቅ በቂ ምክንያት ሆኖ ነበር።
የኢመየብማ ሕልውና እውን የሆነው እንዲህ ባለው ሁኔታ ውስጥ ነበር። መስማት የተሳናቸው ሰዎች ለመብቶቻቸው ሊከራከሩ የሚችሉበት አንድ ማኅበር ያስፈልግ ነበር።

ንቃተ ሕሊናቸው የዳበረ መስማት የተሳናቸው ሰዎች አንድ ማሕበር እንዲመሠረት ለማድረግ ይንቀሳቀሱ ነበር። በወቅቱ ማህበር ማቋቋም በጣም አደገኛ ሥራ ነበር። ወቅቱ ማንኛውም ዓይነት ማኅበራት መንግሥት ጥርጣሬ የሚያይበት ጊዜ ነበር። መስከረም 3 ቀን 1963 ዓ.ም. መስማት የተሳናቸው እና መስማት የተሳናቸው ወዳጆችን ዳግማዊ ምኒልክ አደባባይ አጠገብ በሚገኘው ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ ተሰብስበው ከተነጋገሩ በኋላ ማኅበሩን ለማቋቋም ወሰኑ። (የመሥራች አባሎችን ስም ዝርዝር “ተጨማሪ መረጃ” ተብሎ በመጨረሻ ገጽ ተታይዟል።) ስለሆነም የኢትዮጵያ ማስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኅበር (ኢመየብማ) ተወለደ። ሰባት ሰዎች ያቀፈ አንድ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ (አምስት መስማት የተሳናቸው ወንዶች፣ አንዲት መስማት የተሳናት ሴት እና አንድ የሚሰሙ የምልክት ቋንቋ የሚያውቁ መስማት የተሳናቸው ወዳጅ) ተመርጠዋል።

የኢመየብማ ቦርድ ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣኖችን አቅፎ የነበረ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ስድስቱ ሰሚዎች ሲሆኑ አንዱ ግን መስማት የተሳናቸው ነበሩ። እጅግ ብዙ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ያበረከቱ ሲሆኑ፣ ማኅበራት ለማቋቋም አመቺ ባልነበረበት ወቅት ማኅበሩ ከጥርጣሬ ነፃ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ መልካም ዕድል ፈጥረውለታል። ኢመየብማ የወላጆች ኮሚቴ የነበረው ሲሆን፣ ኮሚቴውም ከወላጆች፣ ከቤተሰብ አባላት እና ከመስማት የተሳናቸው ጓደኞች የተውጣጡ ሰባት አባላትን ያቀፈ ነበር።





(a) የኢመየብማ የመጀመሪያ ቦርድ አባላት፡- ክቡር አቶ አበበ ከበደ ክቡር አቶ ደምሴ አደፍርሰው ክቡር አቶ ተስፋዬ መካሻ አቶ ኃይለማርያም ወልደኪዳን ወ/ሮ አልማዝ ዘውዴ አቶ ወንድምአገኝ አስፋው አቶ ኤሳያስ አስፋው እና ቀጥሎ ደግሞ አቶ ማንእኩልህ ሺፈራው (ፎቶዎች: ከማኅበሩ መዝገብ ቤት)

(b) ከወላጆች ኮሚቴ አባሎች አንዳንዶቹ፡- አቶ በየነ በዛብህ መምህሬ ታደሰ አፍራስ አቶ መንግስቴ ተሰማ አቶ ግርማ ፍስሃ አቶ ሰይድ አሊ ወ/ሮ አበበች ታደሰ አቶ ተክለማርያም መኮንን (ፎቶዎች: ከማኅበረ መዝገብ ቤት

የማኅበሩ ቦርድና የወላጆች ኮሚቴ አባሎች

ሁሉም የዕለት ከዕለት ሥራዎች በሥራ አስፈፃሚው ኮሚቴ ይካሄዱ ነበር። የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ደግሞ ከኮሚቴውአቅም በላይ በሆኑ ጉዳዮች፣ የመንግሥት ፖሊሲ እና ሌሎች ጉዳዮች ከማኅበሩ ቦርድ የተለያዩ መመሪያዎችና ምክር ያገኝ ነበር።



የመጀመሪያው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በ1963 ዓ.ም.:- አቶ ኃይሉ የሱነህ አቶ ተስፋዬ አስናቀ አቶ ምናሴ አበራ አቶ ተክለሃይማኖት ደርሶ አቶ አፈወርቅ መንገሻ አቶ ተስፋዬ ባነቲዋሉ ወ/ሪት ስመኝ ወልደብርሃን (ፎቶ: ከተክለሃይማኖት ደርሶ)

ይህ መዋቅር በመስከረም 1967 መንግሥት ለውጥ እስከ ተካሄደበት ድረስ ሥራ ላይ ቆይቷል። ሆኖም የማኅበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ እስከ ነሐሴ 1969 ድረስ አልተቀየረም ነበር።

## የተከናወኑ እንቅስቃሴዎች

በዚህ ጊዜ መስማት የተሳናቸው ሰዎች ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው በሕብረተሰቡ መማር እንደማይችሉ ተደርገው ይታዩ ነበር። ይህ እንደ ነበር የሚያሳይ መስማት የተሳናቸውን ለማመልከት ወይም ለመለየት
ጥቅም ላይ ውሎ የነበረው ቃል የሚያስተላልፈው መልዕክት ነው። ቃሉም ስለ የመስማት ኃይል አለመኖር ሳይሆን ስለ መስማት የተሳናቸው ሰዎች አእምሮ ትምህርት የመቀበል ችሎታ እና አቅም እንደሌለው አድርጎ የሚያመለክት ነበር።

ስለዚህ በኢመየብማ የተከናወነው የመጀመሪያው እንቅስቃሴ መስማት የተሳናቸው ምን ምን ተግባራት ላይ ተሰማርተው እንደሚገኙ ጥናት ማድረግ ነበር። መስማት ለተሳናቸው ብዙ የተለያዩ የሥራ እንቅስቃሴዎች ላይ ተሰማርተው ተገኝተዋል። ከዚህም በላይ ጥቂቶቹ የራሳቸው ድርጅቶች ባለቤቶች ነበሩ፤ እንዲሁም መስማት ለሚችሉ ሌሎች ሰዎችን የሥራ ዕድል ሰጥተው ነበር።

በሕብረተሰቡ የተያዘው የተሳሳተ አመለካከት ለመለወጥ እንዲቻል የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በመስማት የተሳናቸው የተሠሩ (የተመረቱ) ምርቶች የሚታይበት ኤግዚቢሽን ለማዘጋጀት ወሰነ። በዚሁም መሠረት ኤግዚቢሽኑ መስከረም 1964 ዓ.ም. የተካሄደ ሲሆን መስማት የተሳናቸው፣ የመስማት የተሳናቸው ወላጆች፣ ወዳጆቻቸውና የተጋበዙ እንግዶች በተገኙበት በንጉሠ ነገሥቱ ተመርቆ ተከፍቷል። ከመክፈቻው ሥነ ሥርዓት በኋላ ኤግዚቢሽኑ በሕዝብ እንዲታይ ለአንድ ሳምንት ክፍት ተደርጎ ቆይቷል።

በኤግዚቢሽኑ ላይ በተለያዩ የሥራ መስኮች የተሰማሩ መስማት የተሳናቸው ተሳትፈዋል። ከነዚህም መካከል የሥነ-ጥበብ ባለሙያዎች፣ የወርቅና ብር አንጠረኞች፣ አናፂዎች፣ የልብስ ስፌት ድርጅት ባለቤቶች እና ልብስ ሰፊዎች፣ የጫማ ፋብሪካ ባለቤት፣ ወዘተ. ነበሩበት።



(a) ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ኤግዚቢሽኑን ከከፈቱ በኋላ ከኢመየብማ መሥራቾች አንዱ እና የጫማ ፋብሪካ ባለቤት የሆኑትን አቶ በየነ ከበደን መግለጫ ሲያዳምጡ ይታያሉ። ክቡር አቶ አበበ ከበደ (በስተግራ ጥግ) የኢመየብማ በርድ ሊቀመንበር እና አቶ ኃይሉ የሱነህ የኢመየብማ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር ሲመለከቱ ይታያሉ። መስከረም 1964(ፎቶ: ከማኅበሩ መዝገብ ቤት)



(b) 1964 ዓ.ም.:- ልዕልት ተናኘ ወርቅ የተስፋዬ ባንቲዋሉ የወርቅና ብር ሥራዎች፣የአቶ ጌታሁን ከበደ ቡፌና ሌሎች እንጨት ሥራ ውጤቶች ሲጎኙ፤ በሁለቱ መካከል ወይዘሮ አበበች ታደሰ፣ የወላጆች ኮሚቴ አባል ይታያሉ። (ፎቶ: ከማኅበሩ ስብስብ)

በኢመየብማ ኤግዚቢሽን ላይ

## ዕርዳታ የማግኘት ችግር



መስማት የተሳናቸው የተሰማሩባቸው የሥራ እንቅስቃሴዎች ጥናትን ተከትሎ ማኅበሩ በቆዳ እና በእንጨት ሥራ አነስተኛ የማምረቻ ድርጅቶች ለማቋቋም የሚያስችሉ ሁለት ፕሮጄክቶች አዘጋጅቶ ነበር። እነዚህ ፕሮጄክቶች መስማት ለተሳናቸው የሥራ ዕድል ለመፍጠርና ሌሎች ተመሳሳይ ሥራዎችን ለማካሄድ እንዲቻል ለማኅበሩ አንዳንድ ገቢዎችን እንዲያስገኙ ታስበው የተዘጋጁ ነበሩ። ነገር ግን በሚያሳዝን ሁኔታ በገንዘብ እጥረት ምክንያት ፕሮጀክቶቹን ተግባራዊ ማድረግ ሳይቻል ቀርቷል።

ማኅበሩ ምንም ዓይነት አስተማማኝ የገቢ ምንጭ አልነበረውም። ብቸኛው የገቢ ምንጭ የአባልነት መዋጮ ብቻ ነበር። ነገር ግን የአባሎቻችን የአባልነት መዋጮ የመክፈል አቅም እጅግ በጣም ውስን ነበር። ለበርካታ ዓመታት በወር አንድ ብር (ብር 1.00) ሆኖ የቆየ ሲሆን፣ ይህም በጣም አነስተኛ ነበር። ብዙዎቹ አባሎቻችን ተቀጥረው የመሥራት ዕድላቸው ጠባብ ስለነበር የአባልነት መዋጮ የመክፈል አቅማቸው ውሱንነት የአባልነት መዋጮው በዝቅተኛነቱ ለረጂም ጊዜ እንዲቀጥል አስተዋፅኦ አድርጎ ቆይቷል።

ማኅበሩ ለአባሎቹ አገልግሎት ለመስጠት የሚችልበት ቋሚ አድራሻ አልነበረውም። ማኅበሩ እንደተቋቋመ በመጀመሪያ አካባቢ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው አዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ውስጥ ይገኝ በነበረው ካፌ ውስጥ ይሰበሰብ ነበር። ከዚያ በመቀጠል ኮሚቴው በሁለት የተለያዩ ቦታዎች ይሰበሰብ ነበር። ከማኅበራችን መሥራቾች አንዱ የሆኑትና እንዲሁም ለማኅበሩ መመሥረት ዋና አነቃቂ እንደ ነበሩ የሚነገርላቸው አቶ

ተስፋዬ ባንቲዋሉ፣ የመጀመሪያው የማኅበሩ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ነበሩ። ሙያቸውም የወርቅና የብር አንጣሪነት ነበር። የመሥሪያና የመሸጫ ሱቃቸውም በጣም አመቺ በሆነው የአቡነ ጴጥሮስ አደባባይ በሚገኝበት አካባቢ የነበረ ሲሆን፣ ይህም አካባቢ የብዙ መስማት የተሳናቸው መገናኛ ነበር። በመሆኑም ኮሚቴው የመሰብሰቢያ ቦታ ባስፈለገው ጊዜ ሁሉ የኮሚቴው አባሎች ሱቃቸው ውስጥ እንዲሰበሰቡ እጆቻቸውን ዘርግተው ይቀበሉዋቸው ነበር።
ሁለተኛው ኮሚቴው አዘውትሮ ይሰበሰብበት የነበረበት ቦታ ደግሞ የማኅበሩ አባሎች ወርሃዊ ስብሰባዎች ያደርጉበት ከነበረው ከሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት አጠገብ ነበር። ይህም ቦታ የመጀመሪያው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ባይሆኑም ቀጥሎ የተመረጠው ኮሚቴ አባል የነበሩት የአቶ ጌታቸው ገብረሕይወት መኖሪያ ቤት ውስጥ ነበር።

ኮሚቴው የራሱ ቋሚ ቦታ እስካገኘበት ጊዜ ድረስ አቶ ጌታቸው ቤት ሲሰበሰብ ቆይቷል። በመሆኑም በቋሚ የሥራ ቦታ እና በገንዘብ እጦት የማኅበሩን እንቅስቃሴዎች ለማካሄድ በጣም ፈታኝ ሆኖ ቀይቶ ነበር። ለአባሎች መደበኛና ቋሚ በሆነ መልክ አገልግሎት መስጠት የተጀመረው የማኅበሩ ቦርድ ለሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሊቀመንበሩ ወርሃዊ ደመወዝ ከተዋህዶ ጥበብ የጃንጥላ ፋብሪካ እንዲከፈል ማመቻቸት ካደረገ በኋላ ነበር። ፋብሪካው መስማት የተሳናቸውን ጨምሮ አካል ጉዳተኞች ቀጥሮ የሚያሠራ ኩባንያ ነበር። በተጨማሪም በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የበጎ አድራጎት ድርጅት ሥር ይተዳደር ከነበረው ማዕከላዊ የብሬይል ቤተ-መጻሕፍት ይገኝበት ከነበረው ሕንፃ ውስጥ አንድ ክፍል ያለው ጽሕፈት ቤት ለማኅበሩ አገልግሎት እንዲሰጠው ተደርጓል። የታይፒስት ደመወዝ ደግሞ ከማኅበሩ ከቦርድ አባሎች አንዱ በነበሩት በክቡር አቶ ደምሴ አደፍርሰው ይከፈል ነበር። ይህ የተደረገው ማመቻቸት በ1966 ዓ.ም. አብዮቱ ከፈነዳ በኋላ ለጥቂት ዓመታት ቀጥሎ ቀይቷል።


አቶ ጌታቸው ገብረሕይወት (ነ.ይ.) መኖሪያ ቤታቸውን ለማኅበሩ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ መሰብሰቢያነት ፍት አድርገዋል። (ፎቶ: ከማኅበሩ ስብስብ)

አብዮቱ በ1966 ዓ.ም. ከመፈንዳቱ ጥቂት ወራት ቀደም ብሎ በማኅበሩ ቦርዱ ሊቀመንበር በኩል ከአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት ሁለት የአከአሲዮኖች ድርሻ ለማኅበሩ እንዲሰጥ መፈቀዱን የሚያበስር መልዕክት ተነግሮ ነበር። የሚያሳዝነው ከአብዮቱ ፍንዳታ በኋላ ድርጅቱ በመንግሥት ንብረትነት በመያዙ ስለ ጉዳዩ ዳግመኛ ምንም ነገር ማኅበሩ አልሰማም። በመሆኑም ማኅበሩ ከንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት አንዳችም ነገር አላገኘም።

ማኅበሩ ከመንግሥት አንዳች ዓይነት ነገር ያልደረሰው የማኅበሩ መሪዎች ምንም ዓይነት ጥረት ባለማደረጋቸው ምክንያት አልነበረም። በወቅቱ ያለ ንጉሠ ነገሥቱ ዕውቅናና ይሁንታ ምንም ነገር ሊደረግ አይችልም ነበር። ለኤግዚቢሽኑ መዘጋጀት አንዱ ምክንያት የንጉሠ ነገሥቱን ትኩረት ለማግኘት እንዲቻል በማሰብ ነበር። ሆኖም ግን ያ ምንም አልሠራም። እናም የጃንሆይ 81ኛ የልደት ቀን ሲከበር መስማት የተሳናቸው እፊታቸው ቀርበው መልካም የልደት ቀን ይሁንልዎት ለማለትና ስጦታም ለማበርክት እንዲፈቀድላቸው ማኅበሩ ጠይቋል።

ስጦታውም የወርቅና የብር ሠራተኛ በሆኑ የማኅበሩ አባል እንዲሠራ አድርጓል። የተሠራው በብር የተለበጡ ሁለት የዝሆን ጥርሶች ሆኖ ከዝሆን ጥርሶቹ ጫፎች ላይ ደግሞ የንጉሠ ነገሥቱ ዘውድ ምስል እንዲንጠለጠል ተደርጎ አምሮ የተሠራ ነበር። ስለ ሁለቱ የአክሲዮኖች ድርሻ ለማኅበሩ መሰጠት የተነገረው ከዚህ ሥነ-ሥርዓት



አንዳንድ መስማት የተሳናቸው፣ የቦርድ እና የወላጆች ኮሚቴ አባላት ከግርማዊነታቸው ጋር። ሐምሌ 1973 (ፎቶ: ከማኅበሩ ስብስብ)

ከጥቂት ወራት በኋላ ነበር።

ማኅበሩ አንድ ክፍል ያለው ጽሕፈት ቤት ካገኘ በኋላ የቢሮ ዕቃዎች ችግር አጋጥሞት ነበር። ችግሩ ሊፈታ የቻለው [የኢትዮጵያ ወታደራዊ እዷለማውታ ማኅበር ???] አንስተኛ ግን በጣም ጠቃሚ የነበረ ዕርዳታ ስላደረገለት ጠረጴዛ፣ ወንበር እና መደርደሪያ ለመግዛት በመቻሉ ነበር። ያን ጊዜ እንደ አሁኑ በበጎ አድራጎትና በልማት የሚሰተፉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አልነበሩም። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጎ አድራጎት ድርጅት ነበር። ይሁን እንጂ እንቅስቃሴዎቹ ዓይነ ስውራን እና አረጋውያን ላይ ብቻ ነበር የሚያተኩሩት። የድርጅቱ እንቅስቃሴ መስማት የተሳናቸውን አያካትትም ነበር። እንደ ዩኤስ ኤይድ፣ ዳኒዳ፤ ፊኒዳ፤ ሲዳ ያሉ የልማት ድርጅቶችም ነበሩ። ነገር ግን በመንግሥት ተለይተው የተመረጡ ፕሮጀክቶችን ብቻ ይደግፉ ነበር። በተጨማሪም ትኩረቱ በሕፃናት ላይ ያደረገ የኖርዌይ የሕፃናት አድን ድርጅት ይንቀሳቀስ ነበር። ነገር ግን ድርጅቱ መስማት የተሳናቸው ሕፃናት አካትቶ ስለመሥራቱ በእርግጠኝነት ለመናገር አይቻልም። ሁኔታው እንደዚህ ያለ የነበረ በመሆኑ ማኅበሩ ከአባልነት ክፍያ ከሚሰበስበው ትንሽ ገንዘብ በስተቀር ምንም የገንዘብ ምንጭ አልነበረውም።

ስለዚህ ማኅበሩ የሙዚቃ ድግስ በማዘጋጀት የመጀመሪያው የገንዘብ ማሰባሰቢያ እንቅስቃሴውን አከናውኗል። የክብር ዘበኛ፤ የምድር ጦር እና የፖሊስ የሙዚቃ ባንዶች በዝግጅቱ ለመሳተፍ የተስማሙ ሲሆን ዝግጅቱ አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ አምባሳደር ትያትር ውስጥ ተካሂዷል። እንደ አለመታደል ሆኖ ለአዳራሽ ኪራይ፣ ለግብር እና ለሌሎች ወጪዎች ከተከፈለ በኋላ የተረፈው ገንዘብ ማንኛውም ፕሮጀክት ለማካሄድ በቂ አልነበረም።



የመጀመሪያዎቹ መስማት የተሳናቸው የሥነ-ጥበብ ተማሪዎች በአዲስ አበባ የሥነ-ጥበብ ትምህርት ቤት ውስጥ የተማሩ (ፎቶ: ከማኅበሩ ስብስብ

ለመስማት ለተሳናቸው ምንም ዓይነት የትምህርት ፖሊሲ ያልነበረ ቢሆንም በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ አንድ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ተቀብሎ ሲያስተምር የቆየ ትምህርት ቤት ነበር። ይህ ትምህርት ቤት የአዲስ አበባ ሥነ-ጥበብ ጥበብ ትምህርት ቤት ነበር። ትምህርት ቤቱ አዳዲስ ተማሪዎችን ይቀበል የነበረው በክረምት ወቅት የአንድ ወር ሥልጠና በመስጠት እና ተስፋ ሰጪ ችሎታ ያላቸውን በመለየት ነበር። ከዚህም በላይ በዚያ ወቅት የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር የውጭ ዜጋ የነበሩ ሲሆን፤ መስማት የተሳናቸው ሰዎች መማር አይችሉም በሚለው አባባል አስተሳሰባቸው የተበከለ እንዳልነበረ መገመት ይቻላል። ስለዚህ አንዳንድ መስማት የተሳናቸው ሰዎች በዚህ መንገድ ተጠቅመው መመዝገብ ችለዋል። ሌሎች ጥቂት መስማት የተሳናቸው ደግሞ በንጉሠ ነገሥቱ ትዕዛዝ እንዲገቡ የተደረጉ ነበሩ። በመሆኑም ማኅበሩ ከአሥር በላይ አባላቱ የሥነ-ጥበብ ባለሙያዎች ናቸው።

በመስማት የተሳናቸው የሥነ-ጥበብ ባለሙያዎች የተሠሩ

የሥነ-ጥበብ ሥራዎች ኤግዚቢሽን በተለያዩ ጊዜያት ቀርበዋል። ኤግዚቢሽን የተካሄዱባቸው ቦታዎች በድሮ አውሮፕላን ማረፊያው አካባቢ ይገኝ የነበረው የአሜሪካ ሕብረተሰብ ትምህርት ቤት፣ ማዘጋጃ ቤት፣ በጎ ተቋም እና በሌሎች ቦታዎች ውስጥ ነበር። ይሁን እንጂ በጎተ ተቋም የተካሄደው ኤግዚቢሽን ብቻ መስማት ለተሳናቸው ባለሙያዎች የተወሰነ ገቢ እንዳስገኘ ይነገራል። ምክንያቱም ዝግጅቱ በደንብ የተደራጀና የመግዛት አቅም ያላቸው ተሳታፊዎች የታደሙበት ስለ ነበረ ነው። እነኚህ ኤግዚቢሽኖች ከገቢው በተጨማሪ የመስማት የተሳናቸው የሥነ-ጥበብ ባለሙያዎችን ችሎታ እና የጥበብ ሥራዎች እንዲታወቁ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

ማኅበሩ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ መስማት ለተሳናቸው ልዩ ፍላጎቶች ላይ አትኩሮት እንዲደረግ ሲቀሰቅስ ቆይቷል። በደርግ ጊዜ ውስጥ ለአጭር ጊዜም ቢሆን የከፍተኛ የደርግ ባለሥልጣኖች እይታ በመሳብ ረገድ የተወሰነ ውጤት አግኝቷል። የሚያሳዝነው ነገር በከፍተኛ አመራሮች ላይ ሁከት የተከተለ ተደጋጋሚ ለውጥ ይደረግ ስለነበር ለማኅበሩ ተሰጥቶ የነበረው ትኩረት ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግአመቺ አልነበረም። ቀደምት መሪዎች ከቦታቸው ከመወገዳቸው በፊት ያስተላለፉዋቸውን ውሳኔዎች በአዲሶቹ እንዲተገበሩ ለማድረግ አስቸጋሪ ነበር።


ዮሐንስ ፀጋዬ ዲፕሎማውን ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሲቀበል። ኅዳር 4 ቀን 1965 ዓ.ም. (ፎቶ: ከማኅበሩ ስብስብ)

ቢሆንም ማኅበሩ ስለ መስማት የተሳናቸው ችግሮችና ፍላጎቶች መጠየቁንና ማሳሰቡን ቀጥሎበታል። ከጥቂት ዓመታት በኋላም የማኅበሩ ጥያቄ ወደ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ለመድረስ ቻለ። ምክር ቤቱም ከአባሎቹ አንዱ የሆኑትን ክቡር አቶ ወሌ ቼኮል ማኅበሩን እንዲጎበኙና ያለበትን ሁኔታ እንዲመለከቱ በማድረጉ፣ የማኅበሩ ሃላፊዎች ማኅበሩ ያለበትን ሁኔታ እና አባሎች ያሉባቸው አሳሳቢ ችግሮች ለማስረዳት ዕድል አግኝቷል።
ይህ ከሆነ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ማኅበሩን በተመለከተ ውሳኔ ማስተላለፉን ማኅበሩ ለማወቅ ችሏል። ውሳኔውም የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር እና የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በየሥልጣኖቻቸው ሥር ለሚገኙ የማኅበሩ ችግሮች ዕርዳታ እንዲያደርጉለት ነው። ከዚያ በኋላ በምክር ቤቱ የተወሰነውን ተግባራዊ እንዲደረግለት ከበታች ሃላፊዎች ጋር እልህ አስጨራሽ ትግል ቀጥሏል።

ማኅበሩ ከሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር ያጋጠመው ችግር አልነበረም። ምክንያቱም የሚኒስቴሩ መሥሪያ ቤቱ ባለሥልጣኖች ሁልጊዜ ከማኅበሩ ጎን የቆሙ ስለ ነበሩ ነው። በመሆኑም በሥሩ ይገኝ በነበረው "የድኩማን ማቋቋሚያ ድርጅት" ይባል በነበረው ድርጅት በኩል ለማኅበሩ ሠራተኞች ደመወዝ ከመክፈል ጀምሮ በተለያዩ ሁኔታዎች ማኅበሩን በመርዳትና በመደገፍ የድርሻውን ተወጥቷል።

ማኅበሩ አጋጥሞት የነበረው ትልቁ ችግር ከከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር የበታች ባለሥልጣናት ጋር የተያያዘ ነው።የመሬት እና የመኖሪያ ቤት ጉዳዮችን ማካሄድ ምን ጊዜም በችግር የተሞሉ እና ለምግባረ ብልሹ ድርጊቶች የተጋለጡ ናቸው።



THE PROVISIONAL MILITARY GOVERNMENT OF SOCIALIST ETHIOPIA
OFFICE OF THE CHAIRMAN OF THE COUNCIL OF MINISTERS

(a) ከኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢ ጽሕፈት ቤት የተፃፈ ደብዳቤ (11 የካቲት 1973 ዓ.ም.) (ፎቶ: ከማኅበሩ ስብስብ)



THE PROVISIONAL MILITARY GOVERNMENT OF SOCIALIST ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT & HOUSING

(b) ከኅብረተሰብአዊት ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር የተጻፈ ደብዳቤ (23 መጋቢት 1975 ዓ.ም.) (ፎቶ: ከማኅበሩ ስብስብ)

ከሚኒስትሮች ምክር ቤትና ከከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር የተጻፉ ደብዳቤዎች

ችግሩ ከፍተኛ ባለስልጣኖቻቸው ያስተላለፏቸውን ውሳኔዎች ተፈፃሚ በማድረግ በኩል የበታች ባለሥልጣኖች ዳተኛ መሆን፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ፋይሎችን ሆን ብለው ይሁን ወይም በስህተት የተቀመጡበት ቦታ ባለመታወቁ አልተገኙም በማለት የውሳኔው ተፈጻሚነት እንዲዳተት አድርገዋል። ምንም እንኳን ውሳኔው በግልጽ ለማኅበሩ ዕርዳታ እንዲደረግለት፣ ማኅበሩ የጠቀመውን ቤትም ከኪራይ ነፃ ይሰጠው ቢልም፣ የቤት ኪራይ እንዲከፍል በተደጋጋሚ ጊዜ ተጠይቆ ነበር።

በዚህ መንገድ ማኅበሩ የመሰብሰቢያ አዳራሽ እና አሁን ጽሕፈት ቤቱ የሚገኝበትን ቤት ማግኘት ችሏል። ሆኖም ግን የሚኒስሮች ምክር ቤት ያፀደቀው ውሳኔ ቤትን ብቻ ሳይሆን መሬትንም ጭምር ለማኅበሩ እንዲሰጥ የሚል ነበር። ይሁን እንጂ ለረጅም ጊዜ አልተፈታም ነበር። በመጨረሻም የማኅበሩ ጽሕፈት ቤት አቅራቢያ የሚገኝ አንድ በታ ተሰጥቶት ነበር። በሚያሳዝን ሁኔታ በገንዘብ እጦት ምክንያት በቦታው ላይ ግንባታ ለማካሄድ አልቻለም ነበር። ስለዚህ የከተማው አስተዳደር መሬቱን መልሶ በመውሰድ ለሌላ አካል አሳልፎ ስለ ሰጠው አሁን መስጊድ ተገንብቶበት ይገኛል።

50ኛ ዓመት

ማኅበሩ ለትርፍ ያልተቋቋመ የመስማት የተሳናቸው ማኅበር እንደመሆኑና የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎችም በመንግሥት በኩል ለመስማት የተሳናቸው መደረግ ያለባቸውን ተግባሮች የሚደግፉ እንደመሆናቸው መጠን መሬትን ለማልማት የተሠጠው የስድስት ወራት የጊዜ ገደብ በማኅበሩ ላይ ተፈጻሚ መሆን አይገባውም፤ በማለት አቤቱታ በማቅረቡ፣ በከተማው አስተዳደር ሌላ ተተኪ መሬት እንዲሰጠው ተወስኗል። ይሁን እንጂ ተተኪው ቦታ ከከተማው መሃል በጣም ርቆ በሚገኘው ቦሌ ቡልቡላ አካባቢ ነው። መስማት የተሳናቸው በከተማው ውስጥ ተበታትነው የሚገኙ ስለሆኑ በቦሌ ቡልቡላ የሚገኝ ቦታ ለሁሉም መስማት ተሳናቸው ሰዎች በቀላሉ ተደራሽ አይደለም። ከዚህም በላይ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በርካታ ተማሪዎች በመስማት ተሳናቸው ሕይወት ላይ፣ በምልክት ቋንቋ፣ በመስማት ለተሳናቸው ትምህርት፣ መስማት ለተሳናቸው የሥራ ቅጥር ሁኔታ፣ እና በሌሎች ማህበራዊ፣ ሥነ-ልቦና እንዲሁም በሌሎች ጉዳዮች ጥናትና ምርምር ያካሂዳሉ። ማኅበሩ አሁን ያለበት ቦታ ለእነዚህ እንቅስቃሴዎች እንዲሁም መስማት ለተሳናቸው በጣም ተዳራሽ በመሆኑ እጅግ አመቺ ነው። ስለዚህ ለማኅበሩ የሚሰጠው ተተኪ ቦታም እነዚህን ነገሮች ግምት ውስጥ ማስገባት ይገባዋል ብሎ ያምናል። ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ማኅበሩ በቦሌ ቡልቡላ የሚገኘውን ቦታ ለመቀበል ሳይችል ቀርቷል። አሁንም ቢሆን ይበልጥ ምቹ በሆነ ቦታ ላይ ቦታ እንደሚሰጠው በተስፋ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል።

## ተጨማሪ መረጃ



(ፎቶ፡ ከማኅበሩ ስብስብ)

### የማኅበሩ መሥራቾች

ኢመየብማን ከመሠረቱት መስማት የተሳናቸው እና የሚሰሙ ጓደኞቻቸው ጥቂቶቹ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ በ1963 ዓ.ም.፤ እነሱም (ከግራ ወደ ቀኝ ሲታዩ) የመጀመሪያው መደዳ፡- [ ? ]፣ ጌታቸው ገብረሕይወት፣ ሕዝቅያስ ተሰማ፣ ምናሴ አበራ፣ ተስፋዬ አስናቀ(የሚሰማ)፣ አፈወርቅ መንገሻ ሁለተናው መደዳ፡- አበበ ጥበበ በኛ፣ ሠሎሞን ታደሰ፣ ጥላሁን ፈረደ፣ ዮሐንስ ገብረማርያም፣ ዳንኤል (ሻፊ) አዳም፣ ተክለሃይማኖት ደርሶ፣ ፍቃዱ ኃይሌ፣ [ ? ]፣ ዶኮ ካብትህይመር፣ ጌታሁን ከበደ ሶስተኛው መደዳ፡- ዮሐንስ ፀጋዬ፣ ብዙአየሁ ታደሰ፣ ዓለምሰገድ አርኣያ፣ ሰጠን በላቸው፣ አበበ ለማ፣ [ ? ]፣ ስመኝ ወልደብርሃን፣ ገነት ጌታቸው፣ ሳባ ገረመው፣ ገነት ሙሉሸዋ፣ አሊማ መሐመድ ከኃላ የቆሙት፡- ጌታቸው አበበ፣ አበበ ዓለማሁ፣ አፈወርቅ ኃይለሥላሴ፣ ይልማ ኃይሉ፣ ኃይሉ የሱነህ፣ በየነ ከበደ፣ ወርቁ ዓለማየሁ

ባህል፣ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ
Culture, Arts and Tourism Bureau

Gold
WATER



# የሳንቲሞች ፍልሚያ



ከሃና አፈወርቅ

September 2, 2022

እንዴት ከረማችሁ ውዶቼ? ይሄው አስፈሪው ኮቪድም እንደምንም ተላምዶን አንተ ትብስ አንቺ ተባብሎ አብሮን ይኖር ጀመረ አይደል እንዴ? ከእኔ ጋርማ ከመላመዱ ብዛት እኮ "ሰላም ነው? ፒስ ነው?" እየተባባልን እንዲሁ ቤት ሳይገባ በውጭ ሞቅ ያለ ሰላምታ እንለዋወጣለን። እንደ ልባም ሴት ባሏ ቂቅ ብሎ ዘንጦ ሲወጣ ማንም "በክፉ ዓይኑ" እንዳያይበት (wink wink) በነጭ ሽንኩርት ያበደ ቋንጣ ፍርፍር ባፍ ባፉ እንደምታጎርሰው እኔም እንዲሁ ኮቪድን በክፉ ዓይኑ እንዳያየኝ በነጭ ሽንኩርት እና ማር ባበደ የፈላ ወተት ትን እስኪለው ባፍ ባፉ እያልኩ ተላምደን ተከባብረን አለን።

እንደው ቀልዱስ ቀልድ ነው አለቅን ስንል ዕድሜ ቀጥሎ የማኅበራችንን 50ኛ ዓመት እንድናከብር ያደረሰን አምላክ ክብር ምስጋና ይድረሰው። እናላችሁ በዚህች አጠር ብላ ትንሽ ረዘም ባለች ጽሑፌ የሳንቲሞቹን ፍልሚያ አስመልክቶ እዚህ ሰሜን አሜሪካ በዲሲ እና አካባቢው የምንገኝ መስማት የተሳነን የENAD ፍሬዎች ያደረግነውን ዱላ ቀረሽ ፍልሚያ በወፍ በረር አስቃኛችኋለሁ።

ጊዜው ልጅ ኮቪድ ብቅ ከማለቷ በፊት እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 2019 ላይ መስማት የተሳናቸው ኢትዮ-አሜሪካውያን በሚገናኙበት የፌስቡክ ገፅ Deaf Ethiopians in America (DEA) ላይ በተለያዩ ርዕሶች ዙሪያ ጦፍ ያለ ውይይት፣ ክርክር ባስ ሲልም ዱላ ቀረሽ እንካስላንቲያ የጦፈበት ወቅት ነበር። በዛው ሰሞንም ENAD በባለቤትነት ለሚያስተዳድረው መዋለ ሕፃናት እድሳት እና ለሕፃናቱ መማሪያ ቁሳቁስ ድጋፍ የእርዳታ ጥያቄ ከተለያዩ ተቆርቋሪ ግለሰቦች የሚቀርብበት አጋጣሚ ነበር። በወቅቱ ግን የተቀናጀ ይሄ ነው የሚባል ዕቅድ አልነበረም። መቼስ በአሜሪካ ውስብስብ የኑሮ ሲስተም ሁሉም ሮጦ አዳሪዎች፣ የቤተሰብ ኀላፊ እና አስተዳዳሪዎች ብሎም አገር ቤት ለሚገኙ ቤተሰቦቻቸው ደጋፊ እና ጧሪዎች ስለሆኑ ሁሉን አቀናጅቶ የማኅበራቸውን ትምህርት ቤት እንዲያድሱ ማስተባበር ብሎም ለአንድ ዓላማ ማሰለፍ አዳጋች ነበር።




ፎቶ:- የሴቶቹ ፉክራና እንጉርጉሮ ከፌስቡክ ገጽ DEA የተወሰደ

በዛው ሰሞን የተወሰኑ ሴቶች የልጆቻቸውን ልደት ለማክበር ይገናኛሉ። አጋጣሚውን ተጠቅመው እንዴት ሁሉን አስተባብረን ለመዋለ ሕፃናት ትምህርት ቤቱ አንድ ነገር ማድረግ እንችላለን ብለው ሲወያዩ በአሜሪካ የሚገኙ ልጆቻቸው የሚማሩባቸው ትምህርት ቤቶች እንዴት fund raise እንደሚያደርጉ የታዘቡትን ልምድ አንስተው ተነጋገሩ። እናም ሀሳቡን ለነሱ እንደሚመች አድርገው አሻሽለው በጊዜ በቡድን የት መቼ እንዴት የሚለውን ዝርዝር ዕቅድ አውጥተው DEA የፌስቡክ ገፃቸውን ተጠቅመው ሴቶቹ ወንዶቹን ለፍልሚያ ግጠሙን በሚል ፉከራ መቀስቀስ ጀመሩ። ወንዶቹም መጀመሪያ ምን አመጡብን ብለው ግራ ተጋቡ ሲቀጥል የፍልሚያው አጨዋወት እና አካሄድ ግልፅ ሲሆንላቸው በሴቶችማ መሸነፍ አይሞከርም በሚል

የወንድነት መንፈስ “እረ ጥራኝ ጫካው እረ ጥራኝ ዱሩን” እያንጎራጎሩ እና ዘራፍ እያሉ አከታትለው የቃላት እና የምልክት ነቆራቸውን ሴቶቹ ላይ ሰነዘሩ። ሴቶቹም የዋዛ አይደሉም “get up stand up get up for your prize” ን እያቀነቀኑ የአፀፋ መልስ ምት ወገባቸውን ይዘው እጆቻቸውን አስረዝመው (ማነው ምላስ ብቻ ነው የሚረዝመው ያለው? ) ጉሽማውን ያዘንቡት ጀመረ።

መቼም ተቀናቃኝ ቡድኖቹ ግልፅ የሆነላችሁ ይመስለኛል። በሴት እና በወንዶች መሀል። አሸናፊው ቡድንም ብዙ ሳንቲም የሰበሰበው ይሆናል። ጉሽማ እና መነቋቆሩ ከMarch 1 እስከ May 30, 2019 የሚቆይ ሆኖ በፊስቡክ ገፁ DEA በኢምቋ፣ በአሜሪካን ምልክት ቋንቋ ፣ በአማርኛ እና በእንግሊዘኛ ተደርጓል።



ዙሩ እየከረረ አንገት ለአንገት ተያይዘው የመጀመሪያ ወር የመጋቢት ሪፖርት ደረሰ። በሪፖርቱም ወንዶቹ በከፍተኛ ነጥብ እየመሩ እንደሆነ ታወቀ። ወንዶቹ አፍ አውጥተው እልል አሉ (የተወካዮቻቸዉን ፎቶ ይመልከቱ)።

ሴቶቹም ምንም እንኳን ቢበሳጬም ነገም ሌላ ቀን ነው በሚለው ተስፋ ለቀጣይ ወር ፍልሚያ የእናት መቀነታቸውን ጠበቅ፣ አንገት ቀና፣ ልብ ደንደን አድርገው በውስጥ እየተመካከሩ የበለጠ እጅ ለእጅ ተያያዙ። እንዲሁ መበሻሸቁ መጎሻሸሙ አንዱ ፆታ የሌላውን ፆታ ጉድ ማጋለጡ እንደቀጠለ የሚያዚያ ወር ሪፖርት ደረሰ። በውጤቱም ሴቶቹ ዙሩን አክረው በከፍተኛ ነጥብ ወንዶቹን ኩም አደረጉ። አሁን ሁለቱም ተፎካካሪ ቡድን አንድ አንድ ነጥብ ይዟል። የሶስተኛው እና የመጨረሻው ወር ውጤት ከቀድሞው ውጤት ጋር አብሮ ተደምሮ አሸናፊውን ይለያል። በመሆኑም እጅግ በጣም ዙሩ ከሮ መበሻሸቁ እና ቲፎዞው ተጠናክሮ አንገት ለአንገት ተያይዘው ግንቦት ወርን ጨርሰው ቅዳሜ June 1, 2019 በቨርጂኒያ ስቴት Alexandria city, old town በተባል ቦታ ሳንቲሞቻቸውን ወደ ወረቀት ብር ቀይረው በአካል ተገናኙ። እንዲሁ በአካልም እየተበሻሸቁ ልባቸው ተሰቅሎ በጉጉት ሲጠብቁት የነበረው ውጤት የሚገለፅበት ሰዓት ደርሶ ሁሉም ትንፋሹን ዋጥ አድርጎ የየቡድኖቹ ተወካዮች ውጤት ሲያቀርቡ መከታተል ጀመረ። በውጤቱም ለምንም አይሆኑም ተብለው በየእቃው እና ቤቱ ሲጠራቀሙ የነበሩ የተሳታፊዎቹ ሳንቲሞች ተደምረው በወንዶች $3699 በሴቶች ደግሞ $3624 በድምሩ $7323 የአሜሪካ ዶላር ለመሰብሰብ ተቻለ።



ፎቶ :-June 1, 2019 ተፋላሚዎቹ በተገናኙበት ጊዜ ከግል ማህደር የተወሰደ

በተመሳሳይ ሁኔታ አገር ቤት የሚገኙ መስማት የተሳናቸው የማህበሩ ተቆርቋሪዎች የአቅማቸውን እጅግ በጣም ደስ በሚል ሕብረት አዋጥተው ከአሜሪካ ወዳጆቻቸው ጋር ተቀናጅተው የመዋለ ሕፃናቱ የእድሳት ሥራ ተጀመረ። በተለይ የተማሪዎቹ መፀዳጃ ቤትና ውሃ ከፍተኛ እድሳት ያስፈልገው ስለነበረ እሱ ላይ ትኩረት ተደርጎ ተሠራ። ያገር ቤቶቹ መስማት የተሳናቸው ከገንዘብ ባሻገር የጉልበት ሥራውን 80% ሸፍነው ድንጋይ ተሸክመው፣ ሲሚንቶ አብኩተው ፣ጣውላ አንጥፈው ፣ ኮርኒስ ሰርተው፣ አፅድተው ፣ቀለም ቀብተው፣ ሥእላትን ሥለው፣ ለጉልበት ሠራተኞች እና በጎ ፍቃደኞች ምግብ አብስለው፣ አብልተው አጠጥተው በከፍተኛ የትብብር መንፈስ እና አገልጋይነት የትምህርት ቤቱ እድሳት ተከናወነ።




ፎቶ :-June 1, 2019 ተፋላሚዎቹ በተገናኙበት ጊዜ ከግል ማህደር የተወሰደ

የሳንቲሞቹ ፍልሚያ መንፈሳችንን ያደሰ እርስ በርስ የበለጠ እንድንተዋወቅ ያስቻለ እና በየቤታችን አነስተኛ ናቸው ብዙም ዋጋ የላቸውም ተብለው የተወረወሩ ሳንቲሞች አንድ ላይ ቢሰባሰቡ ጥቅማቸው ቀላል እንዳልሆነ ያሳየ ደስ የሚል ጨዋታ እና ቁምነገር ነበር። እንግዲህ በቀጣይ በሌላ የሳንቲሞች ፍልሚያ እስከምንገናኝ ማኅበሬን እና አባላቱን እንዲሁም ሠራተኞቹን እንኳን ለኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኅበር 50ኛ የምሥረታ በዓል አደረሳችሁ እያልኩ መልካም ቆይታ እመኛለሁ።

በቸር እንሰንብት።



የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኅበር
Ethiopian National Association of the Deaf

Certificate of Appreciation Given from
የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማህበር
Ethiopian National Association of the Deaf
From Ethiopian National Association of the Deaf
Certificate of Appreciation Given from To Ethiopian Deaf Community Members in USA,
Who Contributed to Support co-action pre-school

**Fro the deaf of NEAD**

1. Abriham Lilay
2. Abdurazak Gudu
3. Kidir Yimamu
4. Abraha Redu
5. Haile Gebeyhu
6. Jona parmuange
7. Behailu Argaw
8. Biruck Nigussie
9. Kiberyisfaw Worku
10. Temesgen Adugna
11. Getamesay Mitiku
12. Biruk Woldekidan
13. Mohamed Yasin
14. Yohannes Hailu
15. Tewodros Asefa
16. Abebe Asrat
17. Girmachew Zeihun
18. Jabesa Kebede
19. Fiseha Zewge
20. Abriham Haile (Adullis express INC)
21. Samuel Lelisa
22. Paul Munge Mumina
23. Adiam Asrat
24. Alemaze Gizae
25. Alemtsehay Gizaw
26. Amelework Habtemicael
27. Beliyou Kinfemichel
28. Eteneshe Ayele
29. Enat Hibre
30. Eyerusalem Tsega
31. Eyerusalem Mulugeta
32. Eyerusalem G/Egzabher
33. Genet Asefa
34. Hana Bekele
35. Kidist Lemma
36. Marta Rugassa
37. Meazu Tesfaye
38. Mulualem Gemechu
39. NetsanetUrgassa
40. GabrielaAsres
41. Rebkah Alemayehu
42. Selamawit Fetence
43. Tigist Negash
44. Fanaye Doko
45. Hanna Afework
46. Yebchayensh Asrgachew
47. Rahel Bedada

You all are valuable asset of your Deaf brothers and Sisters learning in our pr-school and your Association. ENAD.

Thanks you so much on behalf of Deaf Children of Co-Action

The President of ENAD
Signature

The director of ENAD
Signature

Amelework Mesfin Zeleke
General Manag

ዳሠሣ

# የኢትዮጵያ የምልክት ቋንቋ (ኢ.ም.ቋ.) አጭር ታሪክ

ዶ/ር ጳውሎስ ካሱ

ከመስማት የተሳናቸው ትምህርት ቤቶች መከፈት ቀደም ብሎ ኢትዮጵያውስጥ መስማት የተሳናቸው ማኅበረሰብና የምልክት ቋንቋ እንደ ነበረ የሚጠቁሙ በጽሑፍ ያልሠፈሩ የተወሰኑ መረጃዎች አሉ። በ1950ዎቹ አጋማሽ ላይ ከሰሜን አሜሪካና ስዊድን የሙጡ ሚሲዮናዊያን በአዲስ አበባና በከረን (በቀድሞዋ የኢትዮጵያ ግዛት ኤርትራ) የመጀመሪያዎቹን የመስማት የተሳናቸው ትምህርት ቤቶች ከፈቱ፡፡ በ1956 ዓ.ም ትምህርት ቤታቸውን በአዲስ አበባ የከፈቱት አሜሪካውያን በማስተማሪያነት የተጠቀሙት ቋንቋ በወቅቱ በጥሩ የዕድገት ደረጃ ላይ የነበረውን የአሜሪካን የምልክት ቋንቋ ሲሆን፣ በከረን ውስጥ ትምህርት የጀመሩት ስዊድናውያን ደግሞ የኖርዲክ ሀገራት የሚጠቀሙበትን አሁን የስውዲን የምልክት ቋንቋ በመባል የሚታወቀውን ነበር። በሁለቱ የምልክት ቋንቋዎች መካከል ልዩነት ቢኖርም፣ በኢትዮጵያውያን ተማሪዎቻቸው ሁለቱም እኩል ተቀባይነት አግኝተው የአሜሪካኑ በመሐል ሀገር፣ የስውዲኑ በሰሜን ኢትዮጵያ በሥፋት ጥቅም ላይ ውለው እንደ ነበረ የወቅቱ ተማሪዎች ይናገራሉ። በምልክት ቋንቋ በመማር የመጀመሪያዎቹ የነበሩት እነዚህ ተማሪዎች ሐሳባቸውን ለመግለጽ በሚያደርጉት ጥረት ውስጥ ዐውቀውም ሆነ ሳያውቁ በአሜሪካና በስውዲን ምልክት ቋንቋዎች ውሥጥ አቻ ለሌላቸው ቃላት የቤት ውስጥ ምልክት ቋንቋ ምልክቶችን እንዲሁም አዳዲስ ሀገር በቀል ምልክቶችን በማስተዋወቅና በሁለቱም የምልክት ቋንቋዎች ውሥጥ ያሉ ምልክቶችን ሀገራዊ ይዘት እንዲኖራቸው አድርገው በመለወጥ ሀገራዊ ሐሳቦችን ለማስተላለፍ በመጠቀም ዛሬ የኢትዮጵያ የምልክት ቋንቋ በመባል ለሚታወቀው ቋንቋ መሠረት ጥለዋል፡፡ በ1960ዎቹ መጀመሪያ ላይ የሁለቱ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች በሥራና በተለያዩ ምክንያቶች መገናኘት ሲጀምሩ፣ የአሜሪካም የስዊድንም የምልክት ቋንቋ ያልሆነ ከላይ የተጠቀሱት ሀገራዊ ምልክቶች ተፅዕኖ ያለበት አዲስ የምልክት ቋንቋ ብቅ ማለት ጀመረ። በሚሲዮናዊያኑ ትምህርት ቤቶች በመማርና የአሜሪካና የኖርዲክ ምልክት ቋንቋዎችን በመጠቀም ስለ ምልክት ቋንቋ ግንዛቤ ያዳበሩት መስማት የተሳናቸው ኢትዮጵያውያን፣ ይህንን ጅምር ሥርዓት ለማስያዝ ሙከራ ማድረግ ጀመሩ። የቤት ውስጥ ምልክት ቋንቋዎችም ሆኑ ከላይ የተገለጹት ጅምሮች የራሳቸው የጣት ፊደላት ስላልነበራቸው ሙከራው ያነጣጠረው የግእዝ ፊደላት አቻ የሆኑ የጣት ፊደላት በመፍጠር ላይ ነበር። አንዳንድ መጣጥፎች ይህንን ወቅት ኢምቋ የተጀመረበት ወቅት አድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ (ይኄይስ፣ 2003)። ይህ ወቅት የኢምቋ የጣት ፊደላት የተጀመሩበት እንጂ ኢምቋ የተጀመረበት ወቅት አይደለም።

በ1964 ዓ.ም አቶ ምናሴ አበራ የተባሉ መስማት የተሳናቸው ግለሰብ ለመጀመሪያ ጊዜ የግእዝ ፊደላት አቻ የሆኑ የጣት ፊደላትን የመፍጠር ሙከራ አድርገው፣ በወቅቱ አጠራር የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ተማሪ ለነበሩት መስማት የተሳናቸው ጓደኛቸው ለአቶ ተክለሃይማኖት ደርሶ ያሳያሉ። ሁለቱ ጓደኛሞች ፈጠራውን በጋራ ካጠኑትና አንዳንድ መሻሻሎችን ካደረጉበት በኋላ የወቅቱ የመስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኅበር ሊቀመንበር ለነበሩት ሌላ መስማት የተሳነው አቶ ኃይሉ የሱነህ የተባሉ ግለሰብ አቀረቡ። አቶ ኃይሉ ለጉዳዩ ትኩረት በመሥጠት ሙከራውን የሚያጠና ሦስት ዓባላትን ያቀፈ የኮሚቴው ዓባላትም እራሳቸው አቶ ምናሴ፣ አቶ ተክለሃይማኖት እና አቶ ኃይሉ ነበሩ። የአቶ ምናሴ ፈጠራ ትኩረት፣ የግእዝ ፊደላትን ቅርጽ በአምስቱ ጣቶች በመሥራት ላይ (ለምሳሌ፡- ሀ፣ ለ፣ ሐ፣ መ፣ ሠ፣ ረ፣ ቀ፣ በ፣ ተ፣ ቸ፣ ኀ፣ ነ፣ ወ፣ ዐ፣ ዘ፣ የ፣ ደ፣ ጀ፣ ጠ፣ ፈ፣ ጸ፣ ፐ)፣ ቅርፃቸውን በአምስቱ ጣቶች መሥራት አስቸጋሪ ለሆኑት ፊደላት ደግሞ ከአሜሪካ የምልክት ቋንቋ የጣት ፊደላት በመዋስ፣ (ለምሳሌ ረ፣ ነ፣ አ፣ ጸ)፣ ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱን መጠቀም አስቸጋሪ በሆኑባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ደግሞ በዘፈቀደ በመፍጠር (ለምሳሌ ሸ፣ ኘ፣ ኸ፣ ዠ፣ ገ፣ ጨ፣ ፀ) ላይ ያተኮረ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ አቶ ምናሴ ለካዕብ፣ ሣልስ፣

ራብዕ፣ ኀምስ፣ ሳድስ እና ሳብእ የፊደል ቁልፎች (አናባቢዎች) አዘጋጅተው ነበር፡፡ "የአንዳንዶቹ ቁልፎች መሠረታዊ ምልክት እስከ 180 ዲግሪ ድረስ ማዞር ያስፈልግ ስለ ነበረ እኔና አቶ ምናሴ ተነጋግረን በአሁኑ ጊዜ ያላቸውን መልክ እንዲይዙ አድርገናል፡፡ ... የግዕዙን ድምፅ የሚወክሉት ላይም በመጀመሪያ አቶ ምናሴ ያዘጋጃቸውን አንዳንዶቹን ለውጠናል፡፡" (ቃለ መጠይቅ፣ ተክለሃይማኖት፣ 2004)፡፡

የአቶ ኃይሉ ኮሚቴ ፈጠራውን ካጠና በኋላ ውጤቱን ለሙከራ አቀረበ፡፡ ሙከራው አጥጋቢ ሆኖ ስለ ተገኘ መስማት የተሳናቸውን ለማስተማር ጥቅም ላይ እንዲውል በማኅበሩ በኩል ለትምህርት ሚኒሥቴር ተላለፈ፡፡ ትምህርት ሚኒሥቴርም መስማት የተሳናቸው ትምህርት ቤቶች አስተያየት እንዲሠጡበት አድርጎ፣ የኀምሃ ደስታ የመስማት የተሳናቸው ትምህርት ቤት ለ "ወ" ተሰጥቶ በነበረው ምልክት ላይ ብቻ ማሻሻያ አቅርቦ ተቀባይነት ስለ አገኘ አሁን ጥቅም ላይ ያለው ምልክት እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ኮሚቴው ማሻሻያውን የተቀበለው የ "ወ" ምልክት ጉድለት ኖሮበት ሳይሆን፣ አብሮ የመሥራት ፍላጎትና ስሜት እንዲዳብር በማለት ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ፈጠራው የትምህርት ሚኒሥቴርን ተቀባይነት እና ድጋፍ ስላገኘ፣ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በሚገኙባቸው ትምህርት ቤቶች በሙሉ ጥቅም ላይ እንዲውል በመላው ኢትዮጵያ ለሚገኙ የትምህርት ቤቶች ጽሕፈት ቤቶች ሰርኩላር ተላለፈ፡፡ አቶ ምናሴ የኢምቋ የጣት ፊደላት የፈጠራ የቅጂ መብት ያልተሰጣቸው ለምን እንደሆነ አቶ ተክለሃይማኖት (2004) እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡ "በወቅቱ አንስቼ የተነጋገርንበት ጉዳይ ነበር፡፡ አቶ ምናሴ ደግና ሩቅ አሳቢ፣ ለወገኖቹ ተቆርቋሪ በመሆኑ፣ ያስብ የነበረው ፈጠራው ለመስማት የተሳናቸው የሚሠጠውን ጥቅም እንጂ የግል ጥቅሙን አልነበረም፡፡ የፈጠራ ቅጂ ለእርሱ ምንም እንዳልነበረ ነበር የነገረኝ፡፡"

የጣት ፊደላቱ ፈጠራ በባዕድ የምልክት ቋንቋ በመማራቸው ባሕላቸውን ለመረዳትና ከማኅበረሰቡ ጋር ለመግባባት ችግር የነበረባቸውን ተማሪዎች ችግር ከመፍታቱም በላይ ብሔራዊ የምልክት ቋንቋ መዝገበ-ምልክት ለማዘጋጀት መሠረት ጥሏል፡፡




የጣት ምልክቶቹ በትምህርት ሚኒሥቴር ተቀባይነት ካገኙ በኋላ የምልክት ቋንቋ መዝገበ-ምልክት ማዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን ማኅበሩ ስለመነበት፣ መዝገበ ምልክት ለማዘጋጀ ጥረት ማድረግ ጀመረ፡፡ በዝግጅቱ ላይ የመስማት የተሳናቸው ትምህርት ቤቶች እንዲሳተፉ ለማድረግ የግድ ወደ ትምህርት ሚኒሥቴር መሄድ ያስፈልግ ነበር፡፡ በወቅቱ ለዕድገት በኅብረት ዘመቻ፣ አቶ ምናሴ ወደ ደብረብርሃን አቶ ተክለሃይማኖት ደግሞ ወደ አሰላ ዘምተው ስለነበረ፣ ጉዳዩን የመከታተል ኃላፊነት የወደቀው በአቶ ኃይሉ ትከሻ ላይ ነበር (ተክለሃይማኖት፣ 2004)፡፡ በአቶ ኃይሉ ጥረትም በ1968 ዓ.ም በትምህርት ሚኒሥቴር ሰብሳቢነት በተደረገ፣ የሁለቱ የመስማት የተሳናቸው ትምህርት ቤቶች (መካኒሳ እና አልፋ)፣ የመስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኅበር፣ የትምህርት ሚኒሥቴር የልዩ ትምህርት ክፍል ተወካዮች በተገኙበት ስብሰባ ላይ የእነዚህን አራት አካላት ተወካዮችን ያቀፈ ኮሚቴ ተቋቁሞ "የአማርኛ" መዝገበ ምልክት እንዲያዘጋጅ ተወሰነ፡፡ በዚሁ መሠረትም ዘጠኝ አባላት ያሉት ኮሚቴ የተቋቋመ ሲሆን፣ ከአባላቱም ሁለቱ አቶ ተክለሃይማኖት ደርሶና አቶ ኃይሉ የሱነህ ነበሩ፡፡ ኮሚቴው ሲቋቋም አቶ ተክለሃይማኖት ከአሰላ

ወደ አዲስ አበባ የዘመቻ መምሪያ ተመልሰው ስለ ነበረ፣ የኮሚቴው አባል የመሆን ዕድል ሲያገኙ፣ አቶ ምናሴ ግን እሩቅ ስለነበሩ፣ ኮሚቴው ውስጥ አልገቡም። ኮሚቴውም "መስማት የተሳናቸው አዘውትረው የሚጠቀሙባቸውን ምልክቶች በመምረጥ፣ "ዓለም አቀፍ" የሆኑ ምልክቶችን እንዳሉ በመውሰድ በባሕላችን ውስጥ ጎላ ብለው የሚታዩትን መርጦ በማስገባትና ከሰሜን አሜሪካው የምልክት ቋንቋም ጥራትና ተስማሚነት ያላቸውን እንዳሉ በመውሰድ" (ሀ መጽሃፍ፣ 1971 ) በ1968 ዓ.ም ሥራውን አጠናቆ ለትምህርት ሚኒሥቴር አስረከበ። "ከትምህርት ሚኒሥቴር ተወክለው የነበሩት የኮሚቴው ዓባላት በመጽሐፉ ይዘት ላይ ያደረጉት ምንም ዓይነት አስተዋፅዖ አልነበረም" (ተክለሃይማኖት፣ 2004)። ኮሚቴው ሥራውን እንዳጠናቀቀ የአርትዖት ሥራ ለማኅበሩ ተሠጠ። የሥዕል ሥራውም ማኅበሩ ባለሙያ ፈልጎ እንዲያሠራ ስለተባለ፣ ማኅበሩ ከዓባላቱ መካከል ሠዓሊ አቅርቧል። ለሠዓሊው የሚከፈለውን ዓበል ሁለቱ ትምህርት ቤቶች እንዲሸፍኑ ሲደረግ፣ ትምህርት ሚኒሥቴር ደግሞ የመማሪያ መጽሐፍ እንደሚያሳትመው፣ ሁሉ መዝገበ ምልክቱንም እንዲያሳትም ኮሚቴው ተስማማ።




1ኛ መጽሐፍ የመጀመሪያው መዝገበ-ምልክት (1972 ዓ.ም)

ከሦስት ዓመታት በኋላ በ1971 ዓ.ም "የአማርኛ የምልክት ቋንቋ መስማትና መናገር ለተሳናቸው፣ ሀ 1ኛ መጽሐፍ" የሚል ርእስ የተሠጠው 15 ምዕራፎችና የአንድ ሺ ዘጠኝ ምልክቶች ሥዕልና 270 ያህል ሥዕል አልባ የምልክቶች መግለጫ የያዘ የመጀመሪያው መዝገበ-ምልክት ታትሞ ወጣ፡ ፡ መዝገበ ምልክቱ የሐረግና የሥዕል መግለጫዎች እንዲሁም የድርጊትና የአቅጣጫ ማመልከቻ መስመሮችና ቀስቶች የነበረው ስለ ነበር ለመረዳት ቀላል ነበር። የዝግጅቱ ዓላማም መስማት የተሳናቸውን "ለመርዳት የሚሹ ሁሉ እንደ መንደርደሪያ ሆኖ እንደሚረዳቸውና በተለይም ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር መነጋገር እንዲችሉ" ታስቦ ነበር።

ይህ የመጀመሪያው መዝገበ ምልክት ለምን "የአማርኛ ምልክት ቋንቋ" እንደ ተባለ ከአዘጋጆቹ አንዱ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡-

ዋነኛው ምክንያት በወቅቱ አዘጋጆቹ ስለ ምልክት ቋንቋ የነበረን ዕውቀት ውሱን መሆኑ ነበር። በወቅቱ እንጠቀምበት የነበረው በሰሜን አሜሪካና በስውዲን አገሮች ውስጥ ይኖሩ የነበሩ መስማት የተሳናቸው የሚጠቀሙባቸውን የምልክት ቋንቋዎች ሲሆኑ፣ በመጽሐፍ መልክ ሲመጡ ደግሞ ፍቻቸው በእንግሊዘኛ ቋንቋ ነበር። ስለዚህ ይታወቁ የነበሩት የእንግሊዝኛ ምልክት ቋንቋ ተብለው ነበር፡ ፡ ፍቻቸው በእንግሊዘኛ ቋንቋ በመሆኑ አብዛኞች መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች፣ የመስማት የተሳናቸው ወላጆች እና ሌሎች የምልክት ቋንቋ የመማር ፍላጎት የነበራቸው ኢትዮጵያውያን በመጽሐፉ ለመጠቀም አይችሉም ነበር። የምልክት ቋንቋ መዝገበ ምልክት ለማዘጋጀት ስንነሣ ዋነኛ ዓላማችን ይህንን ችግር በመፍታት መጽሐፎቹ በሁሉም ሰው እጅ እንዲገቡና ቋንቋው እንዲስፋፋ በማድረግ ላይ ያተኮረ ነበረ። የመጽሐፉን ርእስ አማርኛ ያልነው ምልክቱ አማርኛ ነው ለማለት ሳይሆን የመዝገበ ምልክቱ መግለጫዎች እንደ ሌሎች በእንግሊዘኛ ሳይሆኑ በአማርኛ መሆናቸውን ለመጠቆም ነበር። (ተክለሃይማኖት፣ 2004)

የዚህ መዝገበ-ምልክት ህትመት ለኢምቋ ዕውቅናና ተቀባይነት እንዲሁም መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል። ከመዝገበ-ምልክቱ ህትመት በኋላ ኢምቋ መስፋፋትና ማደግ ጀመረ። ይህንኑ ተከትሎም መዝገበ-ምልክቱ የያዛቸው ምልክቶች

በአብዛኛው ከአሜሪካና ከስዊድን የምልክት የቋንቋዎች የተወሰዱ ስለሆኑ፣ የመዝገበ-ምልክቱ ርዕስም የኢትዮጵያ ሳይሆን የአማርኛ የምልክት ቋንቋ ስለሚል፣ የተዘጋጀውም ጉዳዩ በቀጥታ በሚመለከታቸው መስማት የተሳናቸው ባለመሆኑ መሻሻል አለበት የሚል አቋም በተጠቃሚዎቹ ዘንድ መንፀባረቅ ጀመረ። ሆኖም ሐሳቡ የሁሉም ድጋፍ ስላልነበረውና የመስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኅበርም ካለ መንግሥት ድጋፍ መዝገበ-ምልክት የማዘጋጀት አቅም ስላልነበረው እስከ 2000 ዓ.ም ድረስ ዕቅዱ እውን አልሆነም።

ለሁለተኛ ጊዜ የኢትዮጵያ የምልክት ቋንቋ መዝገበ ምልክት የማዘጋጀት ሙከራ የተደረገው ከ18 ዓመታት በኋላ በ1980ዎቹ አጋማሽ ላይ በመንግሥታዊ ዐካል ነበር። በ1986 ዓ.ም. በሙያና ልዩ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ማስተባበሪያ፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ቡድን ረቂቁ ተዘጋጅቶ በትምህርት ሚኒሥቴር የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት ሚያዝያ 1990 ዓ.ም የታተመው (በኮምፒውተር ተባዝቶ በእጅ ነው የተጠረዘው) ይህ መዝገበ ምልክት "የምልክት ቋንቋ መዝገበ ቃላት፣ ሁለተኛ መጽሐፍ" የሚል ርእስ ያለው ሲሆን 1314 ምልክቶች አሉት። ዝግጅቱ ከጅምሩ የቋንቋውን ባለቤቶችና ማኅበሩን ባለማካተቱ መዝገበ ምልክቱ በመስማት የተሳናቸው ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም።

በ1994 ዓ.ም የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኅበር የምልክት ቋንቋ ልማት ፕሮጀክት አዘጋጅቶ በፊንላንድ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኅበር በኩል ለፊንላንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒሥቴር አቀረበ። የውጭ ጉዳይ ሚኒሥትሩም ከ85 ሺ ዩሮ በላይ በመለገሱ የመዝገበ ምልክት ማዘጋጀቱ ሥራ በ1994 ዓ.ም ተጀምሮ ከስድስት ዓመታት በኋላ በ2000 ዓ.ም ለኅትመት በቃ። ይህ በኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኅበር በመታተም የመጀመሪያው፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ ግን ሁለተኛ (ሁለተኛው መዝገበ ምልክት ከተቆጠረ ሦስተኛ) የሆነው መዝገበ ምልክት በ25 ርዕሶች ዙሪያ 1322 ምልክቶች የያዙ 464 ገጾች አሉት። ይህ መዝገበ-ምልክት በይዘቱና በዓይነቱ ከመጀመሪያው ወይም ሀ መጽሐፍ በብዙ መልኩ ይለያል። አንደኛ፣ ብሔራዊ ይዘት አለው፣ ርእሱ በትምህርት ሚኒሥቴር እንደ ታተመው መዝገበ ምልክት "የአማርኛ የምልክት ቋንቋ" ሳይሆን፣ "የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ" የሚል ነው። ሁለተኛ ምልክቶቹ የቀረቡት በሥዕል ሳይሆን በፎቶግራፎች ሲሆን፣ እንደ አስፈላጊነቱ ለአንድ ምልክት ከአንድ በላይ ፎቶግራፎች አሉት። ሦስተኛ፣ ቃላቶቹ የተጻፉት በአማርኛና በእንግሊዘኛ ስለሆነ፣ አማርኛ ማንበብ የማይችሉም ሊጠቀሙበት ይችላሉ። አራተኛ፡ ከፊንላንድ የምልክት ቋንቋ መዝገበ ምልክት በተውሶ የተወሰዱ የምልክቶች ክንዋኔ ማመልከቻ ቀስቶች ስላሉት የምልክቶች አሠራርን በቀላሉ መረዳት ይቻላል። አምስተኛ፣ አብዛኞቹ ምልክቶቹ ሀገር በቀል ናቸው። ስድስተኛ፣ ዲዛይኑና ቅንብሩ የተሻለ ነው። ሰባተኛ፡ የሥነ ልሳን ባለሙያዎችን ያካተተ ነበር። በሁሉም መሥፈርቶች ይህ መዝገብ-ምልክት እስካሁን ከታተሙት መዝገበ-ምልክቶቹ ሁሉ የተሻለና በስፋት የተሰራጨ ነው። በመጀመሪያ አካባቢ "የደናቁርት ቋንቋ" በኋላም "የአማርኛ ምልክት ቋንቋ" በሚል መጠሪያ ይታወቅ የነበረው ቋንቋ ዛሬ የሚጠራበትን "የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ" የሚል ስያሜ ያገኘው ከዚህ መዝገበ-ምልክት ኅትመት በኋላ ነው።

በኢምቋ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ሥፍራ ካላቸው ክንውኖች ውስጥ አንዱ በ2000 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋና የመስማት የተሳናቸው ባሕል ጥናት ትምህርት ክፍል መከፈቱ ነው። ይህ የቅድመ ምረቃ መርሐግብር በዓይነቱ በአፍሪካ የመጀመሪያው እንደሆነ ይታመናል። የዚህ ትምህርት ክፍል መከፈት የኢምቋን መማር-ማስተማርና ማስተርጎምን ለማዘመን የሚረዱ ባለሙያዎችን ከማፍራት በተጨማሪ በኢምቋ ላይ ሳይንሳዊ ጥናቶችን ለማድረግና ቋንቋውን ለመሠነድ የሚያስችሉ ምቹ አጋጣሚዎችን ፈጥሯል። በዚህ ትምህርት ክፍል ውስጥ ከመቶ በላይ የቅድመ ምረቃና ከአስር በላይ የድኅረ ምረቃ ጥናቶች የተደረጉ ሲሆን ከእነዚህ ጥናቶች ውስጥ አራቱ በዶክተሬት ደረጃ የተደረጉ ናቸው።




ሁለተኛው መዝገበ-ምልክት (2000 ዓ.ም)

እነዚህ ጥናቶች የኢምቋ የቋንቋ መሥፈርቶችን የሚያሟላና የራሱ የሰዋሰው ስርዓቶች ያሉት ቋንቋ መሆኑን እንዲሁም ከአማርኛም ሆነ ከሌሎች ሀገራዊ ቋንቋዎች የተለየ ቋንቋ መሆኑን ከማረጋገጥ በተጨማሪ በሁሉም የፌድሬሽኑ ክልሎች ውስጥ ከመስማት የተሳናቸው ጋር ለመግባባትና መስማት የተሳናቸውን ለማስተማር በስፋት ጥቅም ላይ እየዋለ እንደሆነ አረጋግጠዋል፡፡ በአሁኑ ወቅትም በትምህርት ክፍሉ ሥር የሚደረጉ ጥናትና ምርምሮች የቀጠሉ ሲሆን ሁሉንም የኢምቋን የሥነ ልሳን ክፍሎች አጥንቶ የመሠነድ ሥራዎች ተጀምረዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ኢምቋ በሁሉም ክልሎች በሠፋት ጥቅም ላይ እየዋለ ሲሆን በተለያዩ አካባቢዎች ያለው የኢምቋ አጠቃቀም ተመሳሳይነት የጎላና ያሉት የምልክቶች ልዩነት ጠባብ በመሆኑ ሁሉም የኢምቋ ተጠቃሚዎች ያለምንም ችግር እየተግባቡበት እንደሆነ የተደረጉ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

# የተርጓሚዬ ሚና፡፡

(በመምህር ሰይፉ ይልማ MA)

(ውድ አንባቢያን ሚና የሚለውን ቃል ከተጠየቀ ሳይሆን ከሥራው አስፈላጊነት አንጻር ታዩልኝ ዘንድ ትለመናላችሁ)




ስለ ተርጓሚ ሥናነሣ በቅድሚያ ስለ ትርጉም ምንነት ማንሣት ያስፈልገን ይሆናል፡፡ ትርጉም ምንድን ነው? ስለምንስ አስፈለገ? ብለን ስንጠይቅ ደግሞ በተጓዳኝ የተለያዩ ቋንቋዎች መኖራቸውን እንረዳለን፡፡ የተለያዩ ቋንቋዎች መኖራቸውን ከተረዳን ዘንድ የተለያዩ ቋንቋዎች እንዴት ሊከሰቱ ወይም ሊኖሩ ቻሉ? ወደ የሚል ጥያቄ እንለጥቃለን "ነገርን ነገር ያነሣዋል" እንዲሉ አበው/እመው ሲተርቱ፡፡ በታሪክ ተመዝግቦ እንደተቀመጠው፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፣

"ምድርም ሁሉ በአንድ ቋንቋና በአንድ ንግግር ነበረች፤ ከምሥራቅም ተነሥተው በሔዱ ጊዜ በሰናዖር ምድር አንድ ሜዳ አገኙ፤ በዚያም ተቀመጡ (ከማን ወገን ናችሁ? ከየት መጣችሁ? እናንተ ጸጉረ ልውጦች አለመሆናችሁ ማረጋገጫው ምንድን ነው? ብሎ የጠየቃቸው ማለቴ ያዋከባቸው አልነበረም)፡፡ እርስ በርሳቸውም ኑ ጡብ እንሥራ በእሳትም እንተኩሰው ተባባሉ (የሥራ ፈቃድ፣ የሙያ ማረጋገጫ ሠርተፍኬት ንግድ ፈቃድ ወዘተ

አልተጠየቁም ይሆን ወይስ እነዚህን ጠያቂ ዐካል አልነበረም?)። ጡቡም እንደ ድንጋይ ሆነላቸው፤ የምድርም ዝፍት እንደ ጭቃ ሆነላቸው። እንዲህም አሉ ኑ ለእኛ ከተማና ራሱ ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ በምድር ላይ ሳንበተንም ስማችንን እናስጠራው አሉ (እዚህ ጋር ደግሞ የቦታ ካርታ፣ የይዞታ ማረጋገጫ፣ ዲጅታል ካርታ፣ የዐየር ካርታ ምናምን ብሎ ነገር አልነበረም ሆሆይ ታድለው!)። እግዚአብሔርም የአዳም ልጆች የሠሩትን ከተማና ራሱ ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ ለማየት ወረደ፤ እግዚአብሔርም አለ እነሆ እነርሱ አንድ ወገን ናቸው፤ ለሁሉም አንድ ቋንቋ አላቸው ይሕንንም ለማድረግ ጀመሩ፣ አሁን ያሰቡትን ሁሉ ለመሥራት አይከለከሉም ኑ እንውረድ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማ ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው። እግዚአብሔርም ከዚያ በምድር ሁሉ በተናቸው። ከተማይቱንም መሥራት ተዉ።" (ኦሪት ዘፍጥረት 11፡ 1-9)

እንግዲህ እነዚያ ራሱ እስከ ሰማይ የሚደርስ ግንብ ይገነቡ የነበሩ ሰዎች ሥራቸውን (ግንባታቸውን ስለምን ተዉት? ብለን ብንጠይቅ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማ ቋንቋቸው ስለ ተደበላለቀ የሚል ምላሽ እዚያው ምዕራፍ ላይ እናገኛለን። ተደበላለቀ ሲባል ብዙ ቋንቋ ሆነላቸው ወይም ሆነባቸው ማለት እንደሆነ ከዐውዱ እንረዳለን። እዚህ ላይ አንዱ የአንዱን ቋንቋ እንዳይሰማ የሚለውን ነጥብ በአንክሮ ልናስተውለው ያስፈልገናል። ለመሆኑ ይህን ጽሑፍ የምታነብ አንተ/አንቺ/ እርስዎ ከተደበላለቀው ቋንቋ የየትኛው ቋንቋ ወገን ነዎት? እንዲያውስ ምልክት ቋንቋ ከተደበላለቁት ቋንቋዎች አንዱ ሊሆን እንደሚችል አስበው ያውቃሉ? ወይም ቋንቋቸው ሲደበላለቅ ለመጀመሪያ ጊዜ ሊግባቡ የሞከሩት ባልዳበረ ምልክት ቋንቋ ሊሆን ይችል እንደነበርስ አስበው ያውቃሉ? ደግሞስ፣ ምናልባት የምልክት ቋንቋ ተርጓሚ ቢኖር የተዉት ግንባታ ሊቀጥልና ሕልማቸው ዕውን ሊሆን ይችል እንደነበር?

በሌላ በኩል ሐዋሪያት የሀገሩን ሁሉ ቋንቋ ይናገሩ ዘንድ የቋንቋ ጸጋ እንደተሠጣቸው በሐዋርያት ሥራ ላይ ተጽፎ እናነባለን። በተሠጣቸው በርካታ ቋንቋ የማወቅ ጸጋ ሕዝቡን በቋንቋው አስተምረውበታል። እንግዲህ እእርስዎ በምልት ቋንቋ መስማት የተሳናቸውን ያገለግላሉ? ከመስማት የተሳናቸው ወገንዎ ጋር በምልክት ቋንቋ ይግባባሉ? ወይስ ለምልክት ቋንቋ ተርጓሚዎች ተገቢውን ቦታ ይሠጣሉ?

እንግዲህ ከላይ የተገለጸው ታሪክ በታሪክነቱ ተዘግቦ ከተቀመጠ ከብዙ ጊዜያት በኋላ፣ ሙሴ የሚባል ሰው ተነሣ ወይም መጣ። ሙሴ እስራኤላውያንን ያገለግል ዘንድ በእግዚአብሔር የተመረጠ ነቢይ የነበረ ሲሆን ዋነኛ ሥራው በፈርዖንና በእግዚአብሔር፤ እንዲሁም በእግዚአብሔርና በእስራኤላውያን መካከል ይደረግ የነበረውን መልዕክት ማስተላለፍ ነበር። በአጭሩ መልዕክት አድራሽ ነበር። ታሪኩ እንዲህ ነው፤ እግዚአብሔርም ሙሴን አለው " ሕዝቤን የእሥራኤል ልጆች ከግብጽ ታወጣ ዘንድ ወደ ፈርዖን እልክሃለሁ፡፡ አለው ሙሴም እግዚአብሔርን፡- ጌታ ሆይ እኔም አፌ ኮልታፋ፣ ምላሴም ጸያፍ የሆነ ሰው ነኝ ትናንት ከትናንት ወዲያ ባሪያህንም ከተናገርኸኝ ጀምሮ አፈ ትብ ሰው አይደለሁም። እግዚአብሔርም የሰውን አፍ የፈጠረ ማን ነው; ዲዳስ፣ ደንቆሮስ የሚያይስ ዕውርስ ያደረገ ማን ነው; እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን; እንግዲህ አሁን ሂድ እኔም ከአፍህ ጋር እሆናለሁ የምትናገረውንም አስተምርሃለሁ አለው። እርሱም በምትልከው ሰው እጅ ትልክ ዘንድ እለምንሃለሁ አለው። ሌዋዊው ወንድምህ አሮን አለ አይደለምን እርሱ ደኅና እንዲናገር ዐውቃለሁ እነሆም ደግሞም ሊገናኝህ ይመጣል። ባየህም ጊዜ በልቡ ደስ ይለዋል አንተምትናገረዋለህ ቃሉንም በአፉ ታደርገዋለህ እኔ ከአፍህና ከአፉ ጋር እሆናለሁ. . . . " (ዘጸአት 4፡10-15)።

እንግዲህ ዓላማችን ታሪክን ማጣቀስ እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ማስተማር እንዳልሆነ ከተረዳችሁልን ዘንዳ ወደ ትንተናው እንገባለን። ይኸውም ሙሴ ሐሳቡን በትክክል ለመግለጽ የሚያዳግተው አፈ ኮልታፋ እንደነበር፤ እግዚአብሔር ደግሞ በደንብ ይናገር የነበረውን አሮንን ሳይሆን ሙሴን መምረጡ አፈ ኮልታፋ መሆን ከመሥራትም አልፎ በእግዚአብሔር ከመመረጥ የማይከለክል መሆኑ፤ እንዲሁም አሮን በታሪክ የተመዘገበ ተርጓሚ እንደነበር ነው።

ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ወደ ዘመናችን አምጥተን ስንተረጉመው ሙሴ መስማት የተሳነቸው ወንድም/እኅቶቻችን የሚወክል ሲሆን፤ አሮን ደግሞ የምልክት ቋንቋ ተርጓሚዎችን ይወክላል። እግዚአብሔር ደግሞ ቀጣሪዎች፣ አሠሪዎች፣ የድርጅት ባለቤቶችና የተለያዩ ሓላፊዎችን ይወክላል።

ሙሴ እኔ አፈ ኮልታፋ ነኝ ቢልም በእግዚአብሔር ተመርጦ መልእክት ከማድረስ ግን አልተከለከለም።

ይህም የሆነበት ምክንያት በወንድሙ አሮን ተርጓሚነት መልእክቱን ማድረስ (ማድረግ የሚገባውን ከማድረግ) ያልተከለከለ መሆኑ። ይህን ጽሑፍ የምታነቡ ወንድም እኅቶች እንዲሁም እመው ወአበው ትምህርት ተምሮና ተመርቆ፣ በሙያ ሠልጥኖ፣ ወይም የጉልበት ሥራ ይሠራ ይሠራ ዘንድ ወደ እናንተ የመጣውን መስማት የተሳነው ወገኖቻችሁን ምን ዓይነት ምላሽ እየሠጣችኋቸው ናችሁ? እንደ እግዚአብሔር ወንድምህ አሮን አንደበት ይሆንሃል (በአስተርጓሚ በኩል) እንግባባለን ብላችሁ ትቀጥሯቸዋላችሁ? ወይስ አፈ ኮልታፋ (መስማት የተሳነህ) ነህና ለሥራው፣ ለድርጅቱ፣ ለፋብሪካው ወዘተ አትሆንም ብላችሁ ታገሏቸዋላችሁ?

እዚህ ላይ ዋነኛ ነጥባችን ከላይ በታሪኩ እንደተገለጸው አፈ ኮልታፋ መሆን (ማለት መስማት መሳን) ዋናውን ሥራ ከመሥራት እንደማያግድና እንደ አሮን ያሉ (ድምጽ መስማት የሚችሉ ሰዎች ወይም የምልክት ቋንቋ ተርጓሚዎች) ሙሴ (መስማት የተሳነው ወገናችን) ሊሠራው ይገባ የነበረን ሥራ መሥራት የሌለባቸው መሆኑን ለማስገንዘብ ነው።

ከላይ የገለጽነው ታሪክ ለዚህ ጽሑፍ እንዲስማማ አድርገን አሳጠርነው እንጂ ሙሉ ታሪኩን ብናነበው ሙሴና አሮን አብረው ወደ ፈርዖን ቢገቡም አንዳችም ቦታ አሮን የሙሴን ንግግር ወስዶ ሲናገር ወይም ሙሴን ወክሎ ሲናገር አናገኘውም። በእግዚአብሔርና ፈርዖን መካከል እንዲሁም በእግዚአብሔርና በእስራኤላውያን መካከል ምልእክቱን ሲያደርስ የምናገኘው መጀመሪያዉኑም በእግዚአብሔር የተመረጠው ሙሴ ነው።

ሐሳቤን ሳጠቃልል፣ ሙሴ አፈ ኮልታፋነቱ ሥራውን በሚገባ ከመሥራት ያላገደው መሆኑ፤ አሮን በታሪክ የተመዘገበ የመጀመሪያ ተርጓሚ መሆኑ ከመረዳታችንም ባሻገር የምልክት ቋንቋ ተርጓሚ ቢኖር የሥናዖር ግንብ ከፍጻሜ ሊደርስ ይችል እንደነበር እናስባለን፡ ፡ ይበልጡንም ሐሳቤን ሳሳጥረው ወይም ሳጠቃልለው ሙሴና አሮን ማለት እኔና አንተ ነን።

# ለፈገግታ

ህመምተኛ - ዶክተር እዴት ነኝ? አሁን
ዶክተር - ጥሩም መጥፎም ወሬ ይዤልህ መጥቻለሁ
ህመምተኛ - መጥፎው ወሬ ምንድ ነው?
ዶክተር - ሁለቱም እግሮችህ መቆረጥ አለባቸው
ህመምተኛ - ኦ አምላኬ፣ ጥሩ ወሬው ታዲያ ምንድን ነው?
ዶክተር - ሚቀጥለው አልጋ ላይ ያለው ታካሚ ነጠላ ጫማህን መግዛት ይፈልጋል።

እናት እና ልጅ ወደ ገበያ ሲወጡ እናት ጠረጴዛው ላይ 5 ብር አስቀምጣ ወጣች ከዚያ ሲመለሱ ልጅ ቀደም ብሎ ይገባ እና 5 ብሩን አንስቶ ይወጣል እናትም ቤት ገብታ ያስቀመጠችውን ብር ልታነሳ ብታይ የለም ከዚያ ልጇ ሲመጣ
እናት - ወስደሀል?
ልጅ - አልወሰድኩም
እናት - ምኑን
ልጅ - አምስት ብሩን

ከአብርሃም አለኸኝ/ማክቤል (ካነበብኩት)

## አርአያዎቻችን

# የመጀመሪያው በቻርተር የተመሠከረላቸው መስማት የተሳናቸው የሒሳብ አዋቂ

እኚህ ሰው "ሰው ሁሉ ቀና ነው" ብለው የሚያምኑ አቶ ተስፋዬ ገድሉ ይባላሉ። ባለታሪካችን የኹለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በሚከታተሉትበት ጊዜ ነበር የመስማት ዕክል የገጠማቸው። ምንም እንኳ የመስማት ዕክል ቢያጋጥማቸውም ትምህርታቸውን ለመቀጠል እንዳይችሉ ግን አልገደባቸውም።
በትምህርት ዓለም በነበሩበት ወቅት የተርጓሚ አገልግሎት ማግኘት ባይችሉም የክፍል ጓደኞቻቸው መምህሩ የተናገረውን በጽሑፍ ገለፃ በማድረግና ከሚይዙት ማስታወሻ እንዲገለብጡ በመፍቀድ ዕገዛ ያደርጉላቸው እንደነበር ከመግለጻቸው ባሻገር የነበራቸው ከፍተኛ የሆነ የማንበብ ልምድ ለዛሬ ስኬታቸው መሠረት እንደጣለ ይገልጻሉ።

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሒሳብ አያያዝ ትምህርት በከፍተኛ ማዕረግ ተመርቀዋል። ድኅረ ምረቃ ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት የነበራቸው ቢሆንም በጊዜው ነፃ የትምህርት ዕድል ባለማግኘታቸው ያገኙ ከነበረው አነስተኛ የመንግሥት ደመዎዝ ላይ ቆጥበው በእንግሊዝ ፓውንድ እየከፈሉ የርቀት ትምህርታቸውን እየተከታተሉ በቻርተር የተመሠከረለት የሒሳብ ዐዋቂ ለመሆን በቅተዋል። በትምህርታቸው ከተመረቁ በኋላ የተሰማሩበት የሥራ መስክ የኦዲት ሥራ በመሆኑ የሥራው መስክ ደግሞ የቡድን ሥራ የሚጠይቅ ነውና ከባልደረቦቻቸው ጋር ለመግባባት እንቅፋቶች ቢኖሩም ከበላይ ዐለቆቻቸው ጀምሮ ለሥኬታቸው አስተዋፅዖ ያደረጉላቸው ሰዎች እንደነበሩም ይናገራሉ።

በፌዴራል ኦዲት መሥሪያ ቤት ውስጥ ከ20 ዓመታት በላይ ያገለገሉ ሲሆን ከእነዚህ ዓመታት ውስጥ ለ5 ዓመታት በዳይሬክተርነት ያገለገሉ ሲሆን በኢትጵያ አካል ጉዳተኞች ብሔራዊ ማኅበራት ፌዴሬሽን በምክትል ዳሬክተርነት በመምራት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ከማበርከታቸው ሌላ በኢትዮጵያ



መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኅበር ደግሞ ለ5 ዓመታት የሥራ አሥፈፃሚ ኮሚቴ ፕሬዝዳንት በመሆን ሠርተዋል ።

አቶ ተስፋዬ ገድሉ መስማት የተሳናቸው ቢሆኑም ከዕድሜ ዕኩዮቻቸው ልቀው የተመሠከረለት ኦዲት ድርጅት ለማቋቋም የበቁ በሙያቸው አንቱታ የተቸሩ ናቸው። ያቋቋሙት ድርጅት በዓለም ዐቀፍ ድርጅቶች ለሚደገፉ፣ ለመንግሥታዊ ድርጅቶች፣ መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶችና ማኅበራት በሒሳብ አያያዝና ተዛማጅ ጉዳዮች የማማከር አገልግሎት በመሥጠት ላይ ይገኛል።

ባለታሪካችን ለዚህ ታላቅ ሥኬት የበቁበትን መንገድ ሲገልፁ የግል ጥረት ትዕግሥተኛ መሆናቸው እንዲሁም ከሥራ ባልደረቦቻቸውና ከደንበኞቻቸው ጋር አዎንታዊ ግንኙት መፍጠራቸው መሆኑን ይገልፃሉ።

በትምህርት ቤት ቆይታቸውና በሥራው ዓለም ያጋጠሟቸውና እያጋጠሟቸው ያሉትን ችግሮች ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ፣ በትምህርት ቤት ቆይታቸው ከላይ የጠቀሷቸው የተግባቦት ችግር የነበረ ሲሆን በሥራ ዓለም ከተሠማሩ ወዲህ ደግሞ፣ "የሥራዬ ፀባይ የቀረበውን ሥራ ለመሥራት ብቻ ሳይሆን

ሥራውን አፈላልጌ ለመምጣት ካለብኝ መስማት ስነት ጋር በተያያዘ ከደንበኞቼ አመኔታ ማጣት ዋነኛ ተግዳሮት ነው።" ይላሉ። በዚህም ሳቢያ ሥራውን ለማምጣት በአነስተኛ የሥራ ጫረታዎች ለመሳተፍ እንደሚገደዱ ገልጸዋል። አቶ ተስፋዬ ገድሉ ከላይ የዘረዘሯቸው ሌሎች ፈተናዎች መንስኤ በማድረግ የሥራ ኃላፊዎቻቸውንም ሆነ ማኅበረሰቡን እንደማይፈርጁ ይገልጻሉ። ምክንያታቸው ሲያብራሩ ማኅበረሰቡ ስለ መስማት የተሳናቸውም ሆነ መስማት የተሳናቸው ስለሚግባቡት ቋንቋ ምንም ግንዛቤ የሌለው በመሆኑ ነው። ለዚህ ችግር ደግሞ ሚዲያዎችና የሚመለከታቸው ዐካላት ከላይ በጠቀሷቸው ተግዳሮቶች ላይ በደንብ ይሠሩ ዘንድ አበክረው ያሳስባሉ።

## የመስማት ስነት ያልገደባቸው ዕጩ ዶክተር



ወ/ሮ ወይንሸት ግርማ ከጊዜ በኋላ የመስማት ዕክል ያጋጠማቸው ሲሆኑ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ምልክት ቋንቋና መስማት የተሳናቸው ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ያገኙ ሲሆን ሁለተኛ ዲግሪያቸው ደግሞ ከሥነ.ልሳን ትምህርት ክፍል አግኝተዋል።

በአሁኑ ወቅት PHD ዲግሪአቸውን ለማጠናቀቅ ለፈተና በመዘጋጀትና አርቲክሎችን ለማሳተም ዝግጅት እያደረጉ ይገኛሉ። ለኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኅበር የሥራ አሠፈፃሚ ኮሚቴ ምክትል ፕሬዝዳንት የብሔራዊ ሴቶችና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፕሮጀክት አስተባባሪ ሆነው ከመሥራታቸው ሌላ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የትርፍ ሰዓት መምህር በመሆኑ ግልጋሎት ይሰጣሉ።

ከዚህምበተጨማሪከውጭአገራትበሚቀርብላቸው ግብዣ መሠረት በወጭ አገር በሚደረጉ የምልክት ቋንቋ ምርምሮች ላይ ንቁ ተሳትፎ እያደረጉ ይገኛሉ፡ ፡

ሴትነታቸው ላይ መስማት መሳን ሲታከልት ነገሮችን ከባድ የሚያረግ ቢሆንም ድፍረትና ትግል ካለ ችግሮችን ማለፍ እንደሚቻልና ደፋር መሆንና መታገል የሕይወት መርሃቸው እንደሆነ ይናገራሉ።

በተለይም መስማት የተሳናቸው ሴቶች የተሻለ ሕይወት መምራት እንዲችሉ ማኅበር ከፍተው የአመራር የሕይወት ክህሎት የስነ.ተዋልዶ ሥልጠናዎችን ለመሥጠት ፕሮጀክቶች በመቅረፅ እየሠሩ ይገኛሉ።

ሰው ሲጥር ፈጣሪም ይጨመርለታል ብለው የሚያምኑት እጩ ዶ/ር ወይንሸት ግርማ ጠንክረው መስራታቸው እንዲሁም የብሔራዊ ማኅበሩ ውስጥ በነበራቸውቆይታበርካታልምዶችመቅሰማቸውንና ብሔራዊ ማኅበሩ ለዚህ ስኬታቸው ታላቁን ሚና መጫወቱን በኩራት ይናገራሉ።

አክለውም ያለንበት ማኅበረሰብ አለመስማት እርግማንና ኃጢአት አድርጎ ከመመልከት አልፎ መስማት አንችልም ስንለው ጆሮሽ የታለ የሚል የበዛበት በመሆኑ ብዙ ተግዳሮቶች እንዳሉ አልሸሸጉም።

በዚህም የመግባቢያ ችግሮች የተቋማት ግልፅ ፖሊሲ አለመኖር ወቅታዊ መረጃ ተደራሽ አለመሆን የትምህርት ጥራት ጉድለት የስልጡን መምህራን እጥረት የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚም እንደልብ አለማግኘት የተግዳሮቶች መንስኤዎች መሆናቸውን በመጥቀስ የሚመለከታቸው ዐካላት ችግሮችን ይፈቱ ዘንድ ያሳስባሉ።

በተጨማሪም ምንም እንኳ ከላይ የተዘረዘሩት የመብት ጥሰቶች ቢኖሩም መስማት የተሳናቸው ዜጎች ተስፋ ባለመቁረጥ ሊታገሉ እንደሚገባና ለራስ ጥረት ሳያደርጉ ማንም የሚደርስ ስለሌለ ወገኖቻቸው ተቋማት እንዳደርሱላቸው ከመጠበቅ ይልቅ ራሳቸው ታግለው ችግሮችን እንዲያስወግዱና ከስኬት ማማ ላይ መድረስ እንድንችል ምክረ ሐሳበቸውን ይለግሳሉ።

# መስማት የተሳናት
# የጋላውዴት ዩኒቨርስቲ ምሩቅ



ወ/ሮ ትዕግስት ነጋሽ ወዳጆ የሁለት ልጆች እናት ናቸው። በአዲስ አበባ ዩቨርስቲ መስማት የተሳናቸው ባሕልና ምልክት ቋንቋ ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ዲግሪአቸውን የሠሩ ሲሆን የድኅረ ምረቃ ዲግሪአቸውን በአሜሪካ አገር በሚገኘው ጋላውዴት ዩኒቨርስቲ በሶሻል ወርክ ለመቀበል በቅተዋል።

ባለታሪካችን የከፍተኛ ትምህርት ዲግሪአቸውን ከመሥራታቸው በፊት በማኅበራችን ውስጥ የሥራ አሥፈፃሚ ኮሚቴ ረዳት ፀሐፊ በአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥር በሚገኘው የሴቶች ዘርፍን በፕሬዚዳንትነት ከመምራታቸው ሌላ የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ መዝገበ ምልክት ሠራተኛ በመሆን እንዲሁም የብሔራዊ ሴቶችና ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፕሮጀክት አስተባባሪ እና የጽ/ቤት ሥራ አሥኪያጅ ሆነው በተለያዩ ወቅቶች አስተዋጽ± አበርክተዋል።

በአሁኑ ወቅት ውሎ መግባቢያቸውን በሀገረ አሜሪካ ሚሪላንድ ግዛት የመሠረቱት ወ/ሮ ትዕግስት ነጋሽ በተመረቁበት የሥራ መሥክ ተሠማርተው በዋሽንግተን ዲሲ የማኅበራዊ አገልግሎት ተወካይ በመሆን በሰው አገልግሎት በመሥራት ላይ ይገኛሉ፡
፡
ይህንንም የስኬት ማማ መቀዳጀት ያስቻላቸው በዋናነት ከምንም በላይ ታጋሽ መሆን ተስፋ ማድረግና እምነት ማሳደር የሕይወት መርሃቸው ሆኖ በመገኘቱ መሆኑን ይገልፃሉ።
በተጨማሪም አሁን የደረሱበት ደረጃ ላይ ለመድረስ የቻሉት ነገሮች አልጋ በአልጋ ሆነውላቸው ሳይሆን በብዙ ትግልና ድካም እንደሆነ ይገልጻሉ።

ድኅረ ምረቃ ትምህርታቸውን አጠናክረው በሚመኙት የሥራ መስክ ለመቀጠር እንዴት ማመልከትና መወዳደር እንዳለባቸው በቂ ግንዛቤ ያልነበራቸው በመሆናቸው ማመልከቻቸው በተደጋጋሚ ውድቅ ተደርጌባቸው እንደነበር ያወሳሉ።

ምንም እንኳ ከሁሉት ጊዜ በላይ የሥራ ቅጥር ጥያቄአቸው ውድቅ ቢደረግባቸውም ለውድቀት የዳረጓቸውን ችግሮች በማጥናትና እርምት በማድረግ ተስፋ ባለመቁረጥ በተደጋጋሚ ማመልከታቸውን ሳያቋርጡ በመቀጠላቸው አሁን ያሉበት ደረጃ መድረሳቸውን በኩራት ይናገራሉ።
ሌላው ደግሞ አሁን እየሠሩ ባሉበት መሥሪያ ቤት ብቸኛ መስማት የተሳናቸው በመሆናቸው የመግባቢያ ችግሮች እንዳሉ በመግለፅ የተግባቦትና ተግዳሮታቸውንም በተለያዩ የተግባቦት ዘዴዎች ማለትም በጽሑፍ፣ በከንፈር ንባብ፣ ምልክት ቋንቋ ከሚችሉት ጋር ደግሞ በምልክት ቋንቋ በመግባባት ለመቅረፍ እንደሚጥሩ ገልጸዋል።

ደግሞም ይላሉ አሜሪካ አገር በማኅበራዊ ኑሮ ዙሪያ ብዙ ችግሮች የሉም። ምልክት ቋንቋ ተደራሽነት ለማስጠበቅ መብት አላቸው። አገልግሎት በሚሰጡበት ጊዜ ግን አስተርጓሚ ለመጠየቅ ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ የላለጉዳዮችን ጥያቄ ለመፈፀም መስተጓጎል እንደፈጠረባቸው አልሸሸጉም።

IOCC®

ዘወትር እግርን በመታጠብና ጫማ በማድርግ በአፈር አማካኝነት የሚመጣውን የዝሆኔ በሽታ እንከላከል።

# እናስታውሳችሁ

ብሔራዊ ማኅበሩ ከተመሰረተ እስካሁን ድረስ በስራ አሰፈፃሚ ኮሚቴ ፕሬዝዳንትነት በሙሉ ጊዜም በውክልና ማኅበሩን ሲመሩ የነበሩና በመምራት ለይ የሚገኙ፡- አቶ ምናሴ አበራ ለረጅም አመታት በፕሬዘዳንትነት ያገለገሉ ሲሆን አቶ አለማየሁ ተፈሪ ለሦስት የስልጣን ዘመን በመምራት ይከተላሉ።



አቶ ኃይሉ የሱነህ



አቶ ምናሴ አበራ



አቶ አውላቸው አድማሱ



አቶ ጌታቸው አርጋው
(ነፍስ ኄር)



አቶ ዓለማየሁ ተፈሪ



አቶ ፍቃዱ አሰፋ (በውክልና)



አቶ ተስፋዬ ገድሉ



አቶ ሲሳይ መንግስቱ



አቶ አበበ ታምራት
(በውክልና)



አቶ ቶፊቅ ሐምዲኑር



ዶ/ር ጳውሎስ ካሡ (አሁን)

የብሔራዊ ማኅበሩ ጽ/ቤት በስራ መሪነትና ስራ አስኪያጅነት በማገልገል አስጸዋጽዖ ያበረከቱና በማበርከት ላይ የሚገኙ የሚከተሉት ናቸው።



አቶ ምናሴ አበራ



አቶ ተክለሀይማኖት ደርሰ



አቶ ዘውዴ ደበበ



አቶ ሠለሞን ተስፋዬ (ነፍስ ኄር)



አቶ ዋሲሁን



አቶ ዓባይ ተስፋዬ



አቶ አለሙ ወርቁ



አቶ ንጉሤ ሞገስ



አቶ አብርሃም ሊላይ



ወ/ሮ ትዕግስት ነጋሽ



አቶ ሀብታሙ ከበበ



ወ/ሮ ቃልኪዳን ጌታነህ



አቶ ባዬ እያሱ



ወ/ሮ ትዕግስት ዓለማየሁ



አቶ አማረ አያሌው



ወ/ሮ አመለወርቅ መስፍን (መስማት የሚችሉ አሁን)

## ለተወሰኑ ወራቶች ስራ አስኪያጅ ሆነው ፅ/ቤቱን በውክልና ያገለገሉ።



ወ/ሮ ሕይወት ጌታቸው



ወ/ሮ ወይንሸት ግርማ



አቶ ቶፊቅ ሐምዲኑር

አቶ እንዳለ ታከለ
(የሚሰማ)

ወ/ሮ ፅዮን ይገዙ

## የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ የጣት ፊደል



## አሜን

ጨልሞብን ሳለ ማለዳ ቀትሩ
ሌቱ አልነጋ ብሎ ቀናት ሲቆጠሩ።
ምልክት ቋንቋችን ያኔ ባይፈጠር
ጨለማ ውስጥ ሆነን ተዳፍኖብን ነበር።
ነጋልን ፊደሉን ሀ ብለን ቆጠርን
ለወግ ለማዕረግ ተጉዘን ደረስን።
ጎልቶ የሚታየው የኔ ጥንካሬ
በምልክት ቋንቋ ፊደል ነው
መቁጠሬ።
አምስት አስርተ ዓመት
ተጉዘሽ
ተጉዘሽ
ለወግ ለማዕረግ ብዙዎች
ያበቃሽ።
አንገቴን ሳልደፋ ቀና ባልኩኝ ዛሬ
የማቱሳላ እድሜ ይስጥሽ ማኅበሬ።
ያለኝን ስሰጥሽ ስጦታ ተቀበይ
መልካም ልደት ስልሽ እስቲ ብቻ
አሜን በይ።
ከንጉሴ ሞገስ (አዝማሪው)

## ሁሉም ሰው እራሱን

ጣትን ቀስሮ ያኛውን ከማለት
በቅድሚያ ማፅዳቱ የራስ አንደበት
ከጉቦ እና ምልጃ ከወገናዊነት
ከገንዘብ ምዝበራ ከስርቆት ቅጥፈት
ይመረጣል ሰዎች ሁሉም ሰው እራሱን
መርምሮ ማወቁ ያለበትን እንከን
አለበለዚያ ግን ያልሁትን አድርጉ ተገባሬን አትዩት
ስሰረቅም ዝም በሉ ስዋሽም እለፉት
ትርፉ ማታለል ነው የእምቧይ ካብ መጫወት
ኧረ ለመሆኑ አደባባይ ውሎው ሲመክሩ ሲዘክሩ
የቀን ሰዎች ብቻ ሁነው የሚቀሩ
ብዛታቸው ታውቋል ታይቷል ማህደሩ
አትቅጠፍ እያሉ ከቅጥፈት አውድማ
በአቅም ኑሩ እያሉ ያላቅማቸው ጮማ
ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ዘረፋ በዘዴ
መድረክ ላይ መሃላ በተግባር ላይ ዳዴ
እያለዋወጡ እየቀራረጡ መንገድ ላሳይ ማለት
ራስን ማታለል ነውና ከንቱነት
ሁሉም ሰው ራሱን ይየው ይፈትሸው
ያለበትን እንከን ያፅዳ ያስተካክለው
የህዝብን አደራ የመንግስት አደራን እንደተቀበሉ
ዓመት ሁለት ዓመት ሳያገለግሉ
መሬት ትጠባለች አይገኝ ቦታ
ጥሩምባው ተነፍቶ ተነግሯል በእምቢልታ
የተሰጠችውን አደራ ዘንግተው
ህሊናቸው ሰክሮ በመንፈስ በለፀገው
ማለት ይይዛሉ ሁሉን እኔ ልፍጀው
ከገቢያቸው በላይ መኖር የሚወዱ፡-
አያዋጣምና ይህ አሰራራቸው
ሁሉም ሰው እራሱን ያፅዳ እንበላቸው
ትንሽ ቆንጠጥ ቆንጠጥ ቆንጠጥ እናርጋቸው
አይሰምርም አሰራር እራስን ሳያጥቡ
የቆሸሸ አካልን ይዘ ማንዣበቡ
በይሆናል በሎ መምከር ከመነሳት
በይሆናል ብሎ መውቀስ ከመነሳት
ራስራ አፅድቶ መቅረብ በአርያነት
ሠበብ እያከሉ መመሪያ እያዘቡ፡
የሚያውረገርጉ የሚያሰናክሉ አሉ እንወቃቸው
ሁሉም ሰው ራሱን ያፅዳ እንበላቸው
የኋላ የኋላ ታሪክ ሲሰናዳ
በየፈርጁ ሲታይ ሲበረበር ጓዳ
የቆሸሸው ሁሉ በጣሙን ሲፀዳ
ደብቁኝ ደብቁኝ ሸሽጉኝ ይመጣል
እኔነትን አውቆ ካሁኑ ገለል
ሁሉም ሰው ራሱን ከተቆጣጠረ
ወሰን ተከበረች አንድነት ዳበረ
አገር ሰላም ሆነች መብትም ጠነከረ።

ግርማ ጋሹ
ከፍኖተ ሠላም መስማት የተሳናቸው ቅርንጫፍ

# ሚዲያዎች ምን አሉ

አቶ ተክለሃይማኖት ደርሶ
እንደላኩልን

## የድሮ ጋዜጦች ስለመስማት የተሳናቸው ምን ያሰራጩ ነበር?

ምንም እንኳን በብዛት ባይሆንም፣ የድሮ ጋዜጦች አልፎ አልፎ መስማት የተሳናቸውን የሚመለከቱ ጽሑፎች ያወጡ ነበር።የዚህች አነስተኛ ጽሑፍ አዘጋጅ ከጋዜጦች ቆርጦ ከሰበሰባቸው ጽሑፎች በጊዜው በመስማት የተሳናቸው ላይ የነበረው አስተሳሰብና የቃላት አጠቃቀም የሚያሳይ፣ እንዲሁም ቀደምት የማኅበራችን መሥራቾችና መሪዎች በተለይ የመስማት የተሳናቸውን ትምህርትና የምልክት ቋንቋ በተመለከተ ያደረጉዋቸውን ትግሎች የሚያሳዩ አቅርቧል።

እነዚህ ጽሕፎች የተገኙት ከፖሊስና እርምጃው፣ ከኢትዮጵያን ሄራልድ እና ከአዲስ ዘመን ጋዜጦች ናቸው። “ወረቀት የያዘውን አይረሳም” እንደሚባለው ጋዜጦቹ እንዚህን ጽሑፎች በማውጣታቸው አሁን እንደገና በማኅበራችን 50ኛው ክበረ በዓል ጊዜ በብርታት መጽሔት እንዲወጡ ለማድረግ ስላስቻሉን ለጋዜጦቹ አዘጋጆች ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

## ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት መስማትና መናገር የተሳናቸው ኢትዮጵያውያን ማኅበር አባሎች ከተቀበሉ በኋላ ለመታሰቢያ ፎቶግራፍ ተነሥተዋል

ይህ ፎቶ ታትሞ የነበረው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ሲሆን ቀኑን ሳልይዝ መቅረቴን ገና አሁን ነው ልብ ያልኩት። በጣም አዝናለሁ። ወሩና ዓመተ-ምሕረቱ ግን ሐምሌ 1965 ነበር።



### ግርማዊ ጃንሆይ ከሶማሊያና ከዛምቢያ መሪዎች መልእክት ተቀበሉ

አዲስ አበባ ፤ (ኢ. ዜ. አ.) ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከዛምቢያ ፕሬዚዴንት ዶክተር ኬኔት ካውንዳና ከሶማሊያ ፕሬዚዴንት ዚያድ ባሬ ዘንድ የተላከ መልእክት ተቀብለዋል ።

ከፕሬዚዴንት ካውንዳ የተላከውን መልእክትበታላቁ ቤተ መንግሥት ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ያቀረቡት በኢትዮጵያ የዛምቢያ አምባሳደር ክቡር ሚስተር ፑቴሆ ኤምአንጉዳ ሲሆኑ ከሶማሊያው ፕሬዚዴንት ዚያድ ባሬ የተላከውን ደግሞ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ያቀረቡት የሶማሊያ አምባሳ

በ፯ኛው ገጽ በ፩ኛው ዓምድ ዞሯል

ጋዜጣው የታተመበት ዕለት አልተያዘም።
ዓመተ ምሕረቱ ግን ሐምሌ 1965 ነው። (ተ.ደ)

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፤ መስማትና መናገር የተሳናቸው ኢትዮጵያውያን ማኅበር አባሎችን ከተቀበሉ በኋላ ለመታሰቢያ ፎቶግራፍ ተነሥተዋል ።

“ነገርን ነገር ያነሳዋል” እንደሚባለው፣ ማኅበራችን ሲቋቋም መስማትና መናገር የተሳናቸው ኢትዮጵያውያን አንድነት ብሔራዊ ማኅበር የሚል ስያሜ ነበረው። በኋላ በ1968 ዓ.ም. ይመስለኛል፣ በወቅቱ የነበሩት የማኅበሩ አመራሮች ስሙ ለአጠራር ስለማይመች በማለት ወደ የኢትዮጵያ ደንቄሮች ማኅበር ቀይረውት ነበር። ከነሱ በኋላ ከነሐሴ 1969 ዓ.ም. አከባቢ ጀምሮ የተተኩት የማኅበራችን አመራሮች ደግሞ የማኅበሩን ስም ወደ የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኅበር ቀየሩት። እስካሁን ድረስም በዚሁ ስም ሲጠራ ይገኛል።

# ዓቃቤ ሕግ አልከሰውም ያለው ዲዳ አደገኛ ሌባ ሆኖ ተገኘ

ይህ ጽሑፍ የተገኘው መጋቢት 30 ቀን 1966 ዓ.ም. ታትሞ ወጥቶ ከነበረው ከፖሊስና እርምጃው ጋዜጣ ነው። ጽሑፉ ብዙ ጉዳዮችን ይነካል። “ዲዳ”፣ “ደንቈሮ”፣ ስለሙብት ማለትም እምነት/ክሕደት ተጠይቆ መልስ መስጠት አስፈላጊነት፤ በሌላ አነጋገር ደግሞ (ጽሑፉ ላይ በግል ባይጠቀስም) በእውነት ለመናገር መሃላ ለመስጠት ስለ እግዚአብሔር ምንነት ለመረዳት በቂ ችሎታ መኖር አለመኖሩ ማረጋገጥ አስፈላጊ ስለመሆኑ፣ ወዘተ.።

**ፖሊስና እርምጃው ጋዜጣ፣ መጋቢት 30 ቀን 1966 ዓ.ም.**

## ዐቃቤ ሕግ አልከሰውም ያለው ዲዳ አደገኛ ሌባ ሆኖ ተገኘ

አንድ ማንነቱን ለመግለጽ የማይችል ዲዳና ደንቆሮ በድሬዳዋና በአካባቢው በመዘዋወር በእንቅስቃሴ ባቡር ላይ ከሚገኝ ከዕቃ መጋዘኖች ከአራት ጊዜ በላይ ልዩ ልዩ ዕቃዎች ሰርቆ በየጊዜው በፖሊሶች እየተያዘ ፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላ ዲዳ በመሆኑ ብቻ በነፃ በመለቀቁ እያደር አደገኛ ወንጀለኛ ሊሆን መቻሉን የምድር ባቡር ፖሊስ ገለጸ ።

ተከሳሹ በግምት የሐያ ዓመት ጐልማሳ ሲሆን በአካባቢው ሰዎች ደጐል በመባል እንደሚጠራ ታውቋል ። ደጐል ከልጅነቱ ጀምሮ ከሰዎች ጋር የሚግባባው በአንዳንድ ጥቅሻዎች በስተቀር የማይናገር ዲዳና ደንቆሮ መሆኑን አብረውት የኖሩት ሰዎች ተናግረዋል ። ተከሳሹ በሐኪምም ተመርምሮ የማይናገርና ጆሮውም የማይሰማ መሆኑን በተሰጠው የምስክርነት ደብዳቤ ለማረጋገጥ ተችሏል ። ይህ ሰው የሌብነት ተግባሩን እየፈጸመ መያዝ የጀመረው ከ፲፱፻፷፪ ዓ. ም. ወዲህ ነው።ተከሳሹ በዚሁ ጊዜ ከድሬዳዋ ወደ ጂቡቲ በመጓዝ ላይ ከሚገኝ አንድ የዕቃ መጫኛ ባቡር ላይ ጋሪውን በመስበር ሰላሳ ኪሎ የሚመዝን ቡና ሰርቆ እጅ ከፍንጅ ባቡሩን በሚቆጣጠሩ ፖሊሶች ተይዟል። ደጐል ይህንን ወንጀል የፈጸመው አንድ በግምት አሥራ ስድስት ዓመት ከሚሆነው ልጅ ጋር እንደነበር ታውቋል ። በዚህም ወንጀል ልጁ በጥፋቱ ወደ ጠባይ ማረሚያ ሲላክ ደጐል

ተከታዩን በ፪ኛው ገጽ ይመልከቱ

## ዓቃቤ ሕግ አልከሰውም ያለው..

ከ፩ኛው ገጽ የዞረ

ግን እንደቡቱ ለመናገር አይችልም በመባል በአቃቤ ሕጉ በኩል ድሬዳዋ ኢሣና ጉርጉራ አውራጃ ፍርድ ቤት ቀርቦ በነፃ አሰናብቶት ነበር ።

እንዲሁም ይኸው ተከሳሽ በነፃ ከተሰናበተ በኋላ ከላይ በተገለጸው ዓመተ ምሕረት ውስጥ ከሌሎች ግብረ አበሮቹ ጋር በመሆን በድሬዳዋ ጣቢያ ላይ የቆመውን አንድ የዕቃ መጫኛ ባቡር ከፍተው ከፍተኛ ግምት ያለው ቡና ሰርቀው ሲሔዱ ተይዘዋል ። በተከሳሹና በግብረ አበሮቹ ላይ ምርመራው በሚገባ ከተጣራ በኋላ ፣ አሁንም ድሬዳዋ አውራጃ ፍርድ ቤት ቀርበው ሌሎቹ እያንዳንዳቸው በአንድ ዓመት እሥራት እንዲቀጡ ሲወሰንባቸው ተከሳሹ ዲዳና ደንቆሮ ነው በመባል ምክንያት ተሰጥቶ በነፃ ተለቋል ። እንዲሁም በ፲፱፻፷፫ ዓ/ ም በድሬዳዋ ከተማ ውስጥ ቆሞ ከነበረ አንድ የሰው ማመላለሻ ባቡር ውስጥ በሌሊት በመግባት ከአንደኛ ማዕርግ መቀመጫዎች ላይ የአራቱን ወንበሮች ልባስ ሰርቆ በፖሊሶች እጅ ከፍንጅ ተይዟል።ተከሳሹ ያሰራረቁንም ሁኔታ ሌሎች ሰዎች ባሉበት በእጁ ምልክት በመስጠት አሳይቷል ። የአውራጃው ፍ/ ቤት አቃቤ ሕግ አሁንም ከላይ የተገለጸውን ምክንያት በመስጠት ተከሳሹ በነፃ እንዲለቀቅ ማዘዛቸው ተገልጿል።

አሁንም ይኸው ተከሳሽ በ፲፱፻፷፬ ዓ/ ም ድሬዳዋ የሚገኘውን የጉምሩክ መጋዘን ሰብሮ ወደውስጥ በመግባት ልዩ ልዩ ዕቃዎችና የቁም ሣጥንቁልፎች ሰርቆ ካመለጠ በኋላ በሌላ ቀን በሰረቃቸው ልዩልዩ የቁልፍ ዓይነቶች በመጠቀም በሩን ከፍቶ ለመስረቅ ሲሞክር እጅ ከፍንጅ መያዙ ተነግሯል ። ከላይ በተገለጸውም ሁኔታ ተከሶ ፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላ ለመቅጣትም ሆነ ለመምከር የማይሰማና የማይናገር በመሆኑ ክስ ሊቀርብበት አይገባም በመባል የምርመራ መዝገቡ በአውራጃው ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ በመዘጋቱ ተከሳሹም በነፃ መለቀቁ ተገልጿል ።

ተከሳሹ አሁንም የሌብነት ተግባሩን ባለማቋረጥ ዕቃዮተጫነበትን ባቡር ጋሪውን ቆርጦ ለመስረቅ ሲሞክር በፖሊሶች እጅ ከፍንጅ ተይዟል ። በዚህም ጊዜ አንድ ከፍተኛ የእንጨት መሰንጠቂያ ብረትና የተሰፉ ጆንያዎች መቅደጃ ልዩ ልዩ ስለቶች በእጁ ተገኝተዋል ። በዚህም ወንጀል ምርመራው ተጣርቶና ተከሳሹም በመደጋገም በዚህ ወንጀል መያዙ ተገልጾ ለድሬዳዋ አውራጃ ፍርድ ቤት አቃቤ ሕግ ቢቀብርም አሁንም ተከሳሹስሙን ለመናገር ካልቻለ ሕጋዊ ሐሳብ ሊሰጥበት አይቻልም በማለት ክሱን መዝጋታቸውና ተከሳሹም እንዲለቀቅ ማዘዛቸው ተገልጧል ።

በመጨረሻም ተከሳሹ ድሬዳዋ ከሚገኘው የምድር ባቡር ኩባንያ ቅጥር ግቢ ውስጥ በሌሊት ገብቶ ከመጋዘን ውስጥ አሥራ አራት ጠርሙሶች ሽቶና ውስኪ ሰርቆ ሲወጣ እጅ ከፍንጅ ተይዟል ። ተከሳሹ በሚያዝበት ወቅት ሾልኮ ወደመጋዘኑ የገባበት ቦታ ጠባብ በመሆኑ ለመሹለክ እንዲመቸው በጠቅላላ ልብሱን አውልቆ እርቃኑን ሥጋውን ሆኖ ነው ። በዚህ ወንጀል ከተያዘ በኋላ የምድር ባቡር ፖሊስ መምሪያ ቤትም የተከሳሹን የወንጀል አሠራር መለዋወጥና አደገኛነት በመገንዘብ መፍትሔ እንዲፈለግለት ለሐረርጌ ጠ/ ግዛት ከፍተኛው ፍርድ ቤት ዐቃብያን ሹም ሕጎች ስለሁኔታው በዝርዝር በመግለጽ አመ

ተከታዩን በ፰ኛው ገጽ ይመልከቱ

ጋዜጣ፡ ርምጃው፡ መጋቢት፡ 30-፯-1966-ዓ-ም

## ዓቃቤ ሕግ አልከሰውም...

ከ፪ኛው ገጽ የዞረ

ልክቷል ። የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ዐቃቤ ሕግ ሁኔታውን በዝርዝር ካጠናው በኋላ ከዚህ ቀደም የተፈጸመውን ሁሉ ተከሳሹ በወንጀሉ እንዲገፋበት የተደረገ ከባድ ስሕተትና ጉድለት ስለሆነ በመጨረሻ በተያዘበት ወንጀል እንዲከሰስ ለአውራጃው ፍርድ ቤት ዐቃቤ ሕግ መምሪያ መስጠቱ ታውቋል ።

በዚሁ መሠረት ተከሳሹ ለመናገር ባይችልም ዳኞቹና ሌሎችም ሰዎች በተገኙበት የፈጸመውን ወንጀል በመምራት እንዲያሳይ ተደርጎ በትክክል ለማሳየት በመቻሉ በመጨረሻ በፈጸመው ወንጀል እንዲከሰስ ተደርጓል ። በክሱም መሠረት ተከሳሹ መስማትና መልስ መስጠት ባይችልም በስርቆት ሊተዳደር የሚችል መሆኑን በሚገባ ተረድቶት ኑሮውን በዚሁ ለመመሥረት ያሰበ መሆኑንፍ/ ቤቱ በመገመት በአንድ ዓመት እሥራት እንዲቀጣ ወስኖበታል ፣ የድሬደዋ አውራጃ ፍ/ ቤት በዚህ ውሳኔው ላይ ተከሳሹ አድራጎቱ እንዲጸጸትበትና እንዲታረም ከባድ ወንጀለኞች ከሚታሠሩበት ለየት ባለ ቦታ እንዲቆይ አዟል ።

ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ

**ልዩ ትምህርት መስማትና መናገር ለተሳናቸው**
**ኃይሉ የሱነህ**

አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ 36ኛ ዓመት ቍጥር 871፣ ዓርብ ኅዳር 18 ቀን 1968 ዓ.ም.

## ልዩ ትምህርት

ዓርብ ኅዳር፡ 18/1968
36ኛ፡ ዓመት ቁጥር 871

# መስማትና መናገር ለተሳናቸው

ከኃይሉ የሱነህ ።

ረቡዕ ኅዳር ፲ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ. ም. ከምሽቱ ፪ ሰዓት ከ፴ ላይ ስለ አምሐ ደስታ የደንቆሮዎች ትምህርት ቤት የሚያሳይ ፊልም ልዩ ትምህርት ለመስማትና መናገር የተሳናቸው በሚል ርእስ በትምህርት ሚ/ር የትምህርትና የዜና ማሠራጫ ክፍል ተዘጋጅቶ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የታየውን ከተመለከቱት ወገኖች አንዱ ነኝ ።

በእውነቱ እንደዚህ የመሳሰለውን ብሔራዊ ጉዳይ ከየተደበቀበት እየፈለጉ ከሕዝቡ ጋር ማስታወቅ የሚደገፍ ተግባር ነው ።

አቶ ደመረ ቸርነት የአምሐ ደስታ የደንቆሮዎች ትምህርት ቤት ሥራ መሪ በሰጡት መግለጫ ላይ የእርሳቸው ድርጅት ብሔራዊ የአማርኛ የጣት ፊደል እያዘጋጀ መሆኑን ተናግረዋል ። ብዙ ጊዜ በዜና ማሠራጫዎች ስለ ልዩ ትምህርት የተሳሳተ መግለጫ ሲሰጥ ለዚያም ማስተባበያ ሲሰጡ ከቆዩት ወገኖች አንዱ እኔ ነኝ።

በኢትዮጵያ ውስጥ በሦስት ልዩ ልዩ ሚሲዮኖች የሚረዱ ሦስት ልዩ ልዩ የደንቆሮዎች ት/ቤቶች አሉ ። እነዚህም ፤

፩/ በሰሜን ኢትዮጵያ ከረን የሚገኘው የፀሐይ መታሰቢያ የደንቆሮዎች ት/ ቤት ፤

፪/ እዚሁ በመኻል ኢትዮጵያ አዲስ አበባ ያሉት ፤

ሀ/ መካኒሣ አካባቢ የሚገኘው የአምሐ ደስታ የደንቆሮዎች ት/ ቤት ፤

ለ/ ቦሌ ወረዳ የሚገኘው የእዝነ ጽሙማን ት/ ቤት ናቸው ።

እነዚህ ት/ቤቶች ከተቋቋሙ ከ፲—፳ ዓመት ሆኖአቸው ሳለ ማንኛውም ትምህርት ሲሰጥ የቆየው በባዕድ ቋንቋ በእንግሊዝኛ በመሆኑ ተማሪዎቹ ባገኙት ዕውቀት ከቤተሰባቸውና ከአካባቢያቸው ጋር ለመግባባት አይችሉም ነበር ። እንዲሁም በሦስቱም ት/ቤቶች የሚጠቀሙበት የምልክት ቋንቋ አንዱ ከሌላው የማይመሳሰል ሲሆን፣ ያንዱ ት/ቤት ተማሪ ከሌላው ት/ቤት ተማሪ ጋር መግባባት አይችሉም ። እንግዲህ ከፋፍለህ ግዛ የሚለው ፍልስፍና በመስማትና መናገር የተሳናቸው ዜጎችም ጭምር ላይ እንዳለ እውነት ነው ። የዚህ ዓይነቱ አሠራር አሁንም አልተስተካከለም ። ይህንና ይህንን የመሳሰሉ ችግሮች ከጓደኞቼ ጋር ብዙ ጊዜ ተወያይተንበት፣ ተማሪዎቹ የአንድ አገር ዜጎች እንደመሆናቸው መጠን ለምን ቋንቋቸው አንድ ዓይነት አይሆንም? ከተማሪዎቹ ቤተሰብስ ሆነ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ስንቱ ነው እንግሊዝኛ ተናጋሪ? ከአካባቢያቸው ጋር ሊግባቡ በሚችሉበት መንገድ ለምን እንዲማሩ አይደረግም? ብለን ትምህርት ሚኒስቴርን ጠየቅን ። በሐሳባችንም የትምህርት ሚኒስቴር መስማማቱን ከተረዳን በኋላ ለዚሁ ሥራ የሚረዳ ብሔራዊ የጣት ፊደል አዘጋጅተን በትምህርት ሚኒስቴር በኩል ወደየትምህርት ቤቶቹ ተልኮ በሥራ ላይ እንዲውል ተደረገ ። ታዲያ አቶ ደመረ እንዳሉት የእርሳቸው ትምህርት ቤት የሚያዘጋጀው የአማርኛ የጣት ፊደል እኛ ካዘጋጀነውና ከሰጠናቸው ይለይ ይሆን? ወይስ ያንኑ በአቶ ምናሴ አበራ፣ በአቶ ተክለ ሃይማኖት ደርሶና በእኔ የተዘጋጀውን ብሔራዊ የጣት ፊደል ማለታቸው ነው? እዚህ ላይ ማስ ሚዲያ የላቲንን የጣት ፊደል በፊልም ቀርያ ሲያቀርብ እንደ አቶ ደመረ አባባል ድርጅታቸው ያዘጋጀውን የአማርኛ የጣት ፊደል ማሳዩት በተገባው ነበር ። በእኛ በኩል የምናውቀውና ልንክድ የማንችለው በቀረበው የጣት ፊደል ላይ አምሐ ደስታ ት/ቤት ወን አሻሽሎ ማቅረቡና እኛም በደስታ የተቀበልነው መሆኑን ነው ።

በዚህ አጋጣሚ ልጠቅስ የምወደው በመስማትና መናገር የተሳናቸው ኢትዮጵያውያን ማኅበር አባሎች በሆኑት ከላይ ስማቸውን በጠቀስኳቸው ሰዎች ተዘጋጅቶ በሥራ ላይ እንዲውል የተደረገው ብሔራዊ የጣት ፊደል ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው ።




በፕሮግራሙ ላይ የቀረበው ዝግጅት እስከዚህም የተማሪዎቹን ሙያና ችሎታ አያሳይም ። በፕሮግራሙ ላይ የተደረገው ጥረት ልጆቹ የድምፅ ልምምድና የንግግር ትምህርት፤እንዲሁም የአማርኛ ትምህርት የሚማሩ መሆኑን ለማሳየት የተደረገ ጥረት ነው ። የ በራስ ተጠልቆ በሁለቱም ጆሮዎች ላይ የሚደረገው መሣሪያ ተማሪዎቹ የማይጠቀሙበት ነገር ግን ት/ቤቱን ጉብኚ ሲመጣ እንደዚህ ይሠራበታል ተብሎ ለማሳያ የተቀመጠ የክት መሣሪያ በ፫ኛው ገጽ በ፭ኛው ዓምድ ዞሯል



# መስማትና መናገር …

ከ፪ኛው ገጽ ከ፩ኛው ዓምድ የዞረ ነው። እንዲሁም የ፩ኛው ክፍል ተማሪ «የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ማነው ? » ተብሎ በተጠየቀ ጊዜ አዲስ አበባ መሆኑን በጥቁር ሠሌዳ ላይ ጽፎ አሳ ይቷል ። ተማሪው የተሰጠውን በሚ ገባ አጥንቷል ፤ ከዚያም በላይ ቢማር ኖሮ የበለጠ እንደሚሠራ አልጠራጠርም ።

በአምኃ ደስታ የደንቆሮዎች ት/ቤት ለጥቂት ዓመታት አስተምሬ ስለ ነበር፤ የተማሪዎቹን ከፍተኛ የትምህርት ፍላጎትና አስተሳሰብ ተረድቸዋለሁ ። ቢማሩ ከማንም አያንሱም ። እንዲሁም በቅርቡ ወደ አውሮፖና አሜሪካ ለሥራ ጉዳይ በሔድኩበት ወቅት የልዩ ትምህርት ድርጅቶችን ጐብኝቼ ነበር። የሁለተኛ ክፍል ተማሪ የሆነችው ሕፃን የምትናገረውን በአምሐ ደስታ የደንቆሮዎች ት/ቤት የሚገኝ የ፰ኛ ክፍል ተማሪ እንኳ እንደ ማይናገር ተገንዝቤያለሁ ። እርግጥ ባለሙት አገሮች የሚገኙ መስማትና መናገር የተሳናቸው ከፍተኛ እንክብካቤ ይደረግላቸዋል ። እኛም በእነርሱ ደረጃ ባንሆንም ባለን እንደ አቅማችን ከሠራን እነዚህ በጣም ወደኋላ የቀሩ ወገኖቻችንን ጠቃሚ ትምህርት መስጠት በቻልን ነበር ።

ትምህርትሚኒስቴርስ ይህንን ፊልም እየደጋገመ በቲ-ቪ- የሚያቀርበው ምን አስቦ ነው? ከሕዝብ ለማስተዋወቅ ከሆነ የከረኑም የቦሌውም ት/ቤቶች ዕድል ቢሰጣቸው መልካም ነው ። እነርሱም በዚሁ ሙያ ተሠማርተዋልና ። በተረፈ እውነተኛውን ልዩ ትምህርት ለማስተዋወቅ እንደሆነ በሠለጠኑት አገሮች የተዘጋጁ ግሩም ፊልሞች ስላሉ እነዚያን ቢያሳዩ ሕዝቡን አስተምሮ ያሉትም ት/ቤቶች እንዲሻሻሉ ማድረግ ይቻላል ።

Mission Uses the desf To Rertain Its Hold
by Teklehaimanot Derso

Ethiopian Herald, Sunday, March 31, 1974

# Mission Uses the deaf To Retain Its Hold

by Tekle Haimanot Derso (HSIU)

**First of all, I would like to commend the Ethiopian Herald for the many articles and letters that are appearing on it for the last month now, articles which advocate controversial opinions. I like the paper now, no matter how far the ideas entertained by the authors of the articles differ from mine, because I feel I am not being dictated into swallowing one side of the story, as was the case before the wind of change started to blow.**

But, the article which appeared in your March 20 issue of the Ethiopian Herald under the heading "Educating the Deaf at Amha Desta School" by a Cheryl Ixyman carried ideas that were very hard for me to either swallow or spit.

The only segment of our population which was not represented during the recent upheaval, in addition to the tillers of the soil and the starving peoples of Tigre, Wollo and the Southern parts of our country which were superficially treated by the advocates of change while busily watching over their salary increments, were the handicapped who were living, and being educated, on alms got from the magnanimous rich of the West for a long time now before the peoples of Tigre and Wollo were included on the list. Thus Cheryl Ixyman's article is the first to appear in your paper since the change. This has compel-

(Contd. on page 4 Col. 4)



# Mission Use

(Contd. from page 2 Col. 4)

led me to say some of the ideas I had been postponing for a long time. Cheryl Ixyman's article touches a minority group which does not have any means of lodging its grievance. But the most shameful thing about the article is that it is based on a false information.

I would like to point to the dear readers of the Ethiopian Herald that most of the students at the Amha Desta School for the Deaf pay, at present, a fee of Eth.$10.00 per month per student. Whether the payment is made for tuition or for other purposes is not important. What is important is the students do pay a fee of $10.00 and that this fact is being withheld from the knowledge of the public. I am sending you photo copies of two receipts from a student of the school whose name will remain between you and me as an evidence. The oldest receipt is dated Miazia /64 and is a receipt for $8.00 (I have deliberately left out the date to safeguard the student). The reason of payment is clearly written as "For school fee". The second receipt is dated —/7/66 (i.e. payment for this month) and is a receipt for $10.00. The school principal has not cared to state what the payment was made for. The student told me that he has lost some but all in all I counted twenty receipts for money that range from $5.00 to $10.00, twelve of the receipts being receipts for $10.00. This student has already paid school fee to the sum of Eth. $217.00.

I wonder with what motive Cheryl Ixyman's article was written? Was the existence of school fees at the Amha Desta School deliberately left out by Miss (Mrs) Cheryl? If so, why? Perhaps she didn't mean any harm by writing that article. She was, perhaps, writing wha information (or rather misinformation) she got from the school authorities.

This is not the only time the school authorities have given a false information to the public. I remember reading a letter in "Yezareitu Ethiopia" written by a certain man (I apologize to the reader, I couldn't remember the name of the writer) about a Fitto Ayano, who is the father of four deaf children. The man in his attempt to help send the deaf children to school, wrote a letter to the Amha Desta School asking for their help to give them education and boarding.

The man wrote in his letter to "Yezareitu Ethiopia" that the director of the school informed him that although they give free education they don't give boarding. This reply was again given at a time when the deaf students of the school were paying a fee of $10.00 per month.

If the dear reader is puzzled it is because he/she does not know the reason for establishing the school. Ato Demere, the school principal once told me while I was collecting information for a term paper I was writing on "Deaf Education in Ethiopia compared to that in other countries", that the reason why the Church of Christ Mission had to start the school for the deaf was that the government authorities told them to start something, such as a clinic, hospital or a school so that they may qualify to start their mission activities in Ethiopia. Ato Demere might say he has not told me so. But he cannot deny the reason for starting the deaf school was in order for the mission to start its activities in Ethiopia. I have got evidence that this is so. These unscrupulous missionaries, and most of their employees, who run the school use the deaf as a publicity issue. They use the deaf as a means of retaining their hold in Ethiopia. Under these conditions any attempt tc teach the deaf is likely to fail as it very well deserves.

The school has just switched to instructing the deaf in Amharic as a face-saving device when it came under criticism from certain quarters. It has made this change without making adequate preparation. It has even gone farther to ask the Ministry of Education and Fine Arts to allow its 6th grade students to sit for the national exams. I again say that it is trying to use the deaf as a publicity issue. It wants to hit headlines as the first deaf school to sit deaf students for the national exams.

The deaf have done no wrong to deserve the penality of sitting for more than three hours at a stretch gazing over examination papers they don't understand anything. Although they are very brilliant students, which I attribute to their own hard work, circumstances have not allowed them to develop language capabilities so they could take the Ministry's exams yet. What effects may it have on their behaviour when they discover that they have got "F" in all the subjects? I hope the Ministry of Education and Fine Arts will refuse to issue

Sunday, March 31, 1974

## ...s the Deaf To Retain ..

such a permit until it satisfies itself that the students have the required knowledge by giving them a mock-up exam.

Cheryl Ixyman, further quotes Ato Demere as saying "The aim of our school is not just to educate the students, but to make them self-supporting and able to cope with the World". How can the deaf "be able to cope with the world" if they are not taught to express their ideas even by writing in correct English or Amharic?, if what they study under the name of vocational agricultural programme is only gardening? I don't, at all, imply that gardening is bad or useless, but what I am saying is that this is not something that could enable the deaf to be self-supporting. They don't have land to practise their acquired knowledge in Addis Ababa. It is, of course, out of the question for the deaf individually to start a farm out of Addis Ababa since this would require knowledge for higher than they could hope to get at Amha Desta School. It would also need much financial outlay to start a farm.

The only teacher at the Amha Desta School who is a qualified teacher according to Cheryle Ixyman's article is Mr. Carl McDonald. All the rest, including the School principal do not even have a diploma or certificate to teach the hearing.

In the Western World, one needs many years of training after qualifying as a teacher of the hearing in order to qualify as a teacher of the deaf. The only mission school for the deaf that has understood this fact is the Princess Tsehai School for the Deaf at Karen in Eritrea which is the oldest deaf school in Ethiopia. (It is 19 years old).

Whenever the authorities of the Amha Desta School expect a visitor, they try to give him a good impression. They have some group hearing-aids and audio-meter. Before their guest arrives they take out these gadgets and harness them to some deaf who could not protest that they are being used as publicity issues. After satisfying their visitor's curiosity that the deaf could indeed understand and be taught by means of these electronic instruments, and after seeing off their guest, they carefully pack away the aids, safely out of reach of the inquisitive touches of the deaf until another prospective visitor phones them his intention of visiting their school.

May be the Amha Desta School for the Deaf is good so long as we don't have deaf children and we are not forced to send our beloved ones to intellectually vegetate under the supervision of unscrupulous people disguised as messengers of God's love. Mr. Editor, should you decide to send one of your reporters to cover the school please warn him not to drink any water at the school for one strong critic of the school has to say this "Amha Desta the place where destitute families pay $10.00 per month so their children can drink infected water."

At last I would like to request (Miss) (Mrs) Cheryl Ixyman to revisit the school and re-examine the information that was given her.

I request her to do it as a special favour to the deaf to whom she has done a great harm by writing that article. Furthermore I request her to interview some deaf students of the school privately. In case she does not know the language of signs, the writter of this article would like to volunteer his free service. Should she prefer to get such a service from a neutral person he would be glad to give her the telephone number of a lady who is an expert at the language of signs.

Thank you.

# Educating the deaf
by Minasse Abera

Ethiopian Herald; Sunday, April 7, 1974

## Educating the Deaf

**I read on one of your issues an article entitled 'Educating the deaf at Amha Desta School' written by Mr. (Mrs) Cherly Ixyman. The writer no doubt has tried in his (her) capacity to inform the public the school's achievements in the past and its future aim toward the deaf.**

However, there are some parts in the article that arose my curiosity and are nudging me to express my mind. I hope that the reader will not take it as if written in disparagement of the author of the article's effort. My first puzzle is why such an article did not come from the school director himself, the assistant, or the mission director since such an article requires their responsibility. I am not saying that the author shouldn't have written that article. In fact every body can express his ideas freely. But I saw in that article that the writer has been misinformed and this I believe can do much harm to the deaf, though the writer's responsibilty lies only in contributing the article.

In his (her) introduction of the school the writer has stated that of the five schools for the deaf available in Ethiopia, the Amha Desta School for the deaf merits special attention. I disagree with this because this will bring to null other missionaries' efforts and it lauds only one particular school which to my knowledge does not know what or how others are teaching let alone compare itself with them and get such a high rating.

According to the writer, at present there are about 60 deaf in the school from grades one to six (I thought there were seven grades!) receiving tuition free with A-I education. As far as I can remember tuition was free before 1963 (E.C.) and later on I have learned that students have started paying from mid 1964(E.C) and that they are still paying.

So, the writer can not say that tuition is free unless the misinformers wanted to hide some of the facts. Another lump in my throat is the A-I rating which the writer described as a citation from the Ministry of Education for its Academic excellence because it has supplemented the required curriculum in the past few years. If the concerned ministry really agrees that the school is following its required curricula, then I will come to think that it knows much about deaf education than I was believing it doesn't and this I think is one tremendous leap on the part of the Ministry which as a matter of fact its office makes it responsible of. I hope the reality would not be a crime on the part of the Ministry to-

(Contd. on page 4 Col. 4)

## Educating the ...

(Contd. from page 3 Col 4)

wards the deaf.

As the writer has stated it is true that a considerable number of its students have left the school. But as far as I can remember most of them did not leave the school with the blessing of being able to finish the limited classes that the school has. Some left because of necessity and some were discouraged. Even most of those who graduated do not show experience of the uplifting sense of Self-worthiness which the writer described as an asset of the school's academic excellence and its experiment in teaching vocational and productive skills which the writer goes on to say that it has reaped positive results.

The writer also quoted the principal as saying 'It is hard to remember the exact number of graduates'. He gave the deaf in the umbrella factory, in a printing shop, and in the Art School as an example of its achievements. But I still do not think that it is that much difficult to guess how many. If I wanted to salt it with too much exaggertion I would simply say fifty. And that number is more than large if it can help us to see what is meant by achievement.

However I must note that I am not trying to blame the school. I know that it is living with its limited capacity and that if it seems has not fulfilled what it ought towards the boys. It has at least given benefits to its girl students which I agree to be taken as an asset.

But what use has (farming) gardening to the boys? Where and how are they going to apply it. One more question. Why did the writer refrain from mentioning the poultry farm in the school when indicating the vocational guidance given there?

*Minasse Abera*

Sunday, April 7, 1974

# ጨዋታ ለልጆች

ፍቃዱ አሰፋ
ካነበብኩት

ጨዋታ የልጆች ቋንቋ መግባቢያ የሀሳብ መግለጫ ስለራሳቸው፣ አካባቢያቸውና ስለዓለም መማሪያ ነው። በተለይ የንግግር ቋንቋ ባልደረሰበት ሁኔታ ጨዋታ የልጆች መግባቢያና ስሜታቸውን መግለጫ በመሆን ያገለግላል። በየትኛውም ዓለም፣ በማንኛውም ሁኔታና ዕድሜ ደረጃ ያለ ልጅ ሁለ ጨዋታ ያግባባዋል። ጨዋታ ለልጆች ሁለንተናዊ እድገት ወሳኝ ከመሆኑም በላይ በተባበሩት መንግሥታት የልጆች መብቶች ኮንቬንሽን እንደ አንዱ የሕፃናት መብት ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

